


# ሊየተና ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

## (አባ ፡ ይባስ)

## ፲፱፻፲–፷፻ ፡ ዓ.ም. ።

## 1

## ትውልድና ፡ እድገት

ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ካባታቸው ፡ ከልጅ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሞላ ፥ ከናታቸው ፡ ከወይዘሮ ፡ ደስታ ፡ (ወሰን ፡ የለሽ) ፡ አባዬ ፥ የይፋት ፡ አውራጃና ፡ የመንዝ ፡ አውራጃ ፡ አዋሳኝ ፡ እኾነው ፥ ጎራት ፡ እተሠኘው ፡ አገር ፡ ላይ ፥ ሚያዝያ ፡ 30 ፡ ቀን ፡ 1910 ፡ ዓ.ም. ፡ ተወለዱ ።

ዘመኑ ፥ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፥ በይፋት ፡ ቈላ ፥ ሕዝብ ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ሚካኤል ፡ ደጋፊና ፡ በራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ደጋፊ ፥ ወገን ፡ የለየበትና ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ የተጣላበት ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ነፍሰ ፡ ጡሯ ፡ ወይዘሮ ፡ ደስታ ፡ አባዬ ፥ የጸጥታውን ፡ መታወክ ፡ በመፍራት ፥ ከቤታቸው ፡ ከመንግሥት ፡ ወደ ፡ ደጋው ፡ ወደ ፡ ጎራት ፡ ወጥተው ፥ እናታቸው ፡ እወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ ረዴ ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፥ ልጃቸውን ፡ በሰላም ፡ ተገላገሉ ።

ሊ.. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ባባታቸው ፡ በልጅ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሞላ ፥ በጠቅላላው ፡ ሸዋ ፡ (ከመርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ አምኀየስ) ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ ግድምና ፡ ኤፍራታ ፡ (ከወልደ ፡ ገብርኤል) ፥ ግሼ ፡ (ከአውሳቤ) ፥ መንዝ ፡ (አፍቀራ ፡ ከጐሌ/ጕልላቴ ፥ ዐራድማ ፡ ከዐስቦ) ፥ ይፋት ፡ (ጨኖ ፡ ከኈሌ) ፥ ተጕለት ፡ (ከይገባዋል) ፥ ወግዳ ፡ (ከኀርያቆስ) ፥ እንዲሁም ፡ መርሐቤቴ ፡ ይወለዳሉ ።

በናታቸው ፡ በወይዘሮ ፡ ደስታ ፡ አባዬ ፥ ይፋት ፡ (ከአቤቶ ፡ ወረደ ፡ ቃል ፡ ሥግወ ፡ ቃል) ፥ ግሼ ፡ (ከአውሳቤ) ፥ መንዝ ፡ (ዐራድማ ፡ ከወልዱ) ፥ ተጕለት ፡ (ከይገባዋል) ፥ ወግዳ ፡ (ከኀርያቆስ) ፥ እንዲሁም ፡ ቡልጋ ፡ ይወለዳሉ ።

ወይዘሮ ፡ ደስታ ፡ አባዬ ፥

- ከመጀመሪያ ፡ ባላቸው ፡ ከቀኛዝማች ፡ አሸኔ ፡ አምበሴ ፥ ፊታውራሪ ፡ ማሞ ፡ አሸኔንና ፡ ወይዘሮ ፡ መድፈሪያሽ ፡ ወርቅ ፡ አሸኔን ፤
- ከኹለተኛ ፡ ባላቸው ፥ ከልጅ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሞላ ፥ ልጅ ፡ አሰፋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፥ ልጅ ፡ ለማ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴንና ፡ ሊ.. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፤
- ከመጨረሻ ፡ ባላቸው ፥ ከባሻ ፡ ግዛው ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድ ፡ ደግሞ ፥ ልጅ ፡ ታደሰ ፡ ግዛውንና ፡ ወይዘሮ ፡ የተሻ ፡ ወርቅ ፡ ግዛውን ፡ ወልደዋል ።

ሊ.. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ገና ፡ በሕፃንነታቸው ፡ ዘመን ፥ ብልኀነትና ፡ ቀናነት ፥ ርኀሩኀነትና ፡ የዋህነት ፥ እልኸኝነትና ፡ ልበ ፡ ሙሉነት ፥ ያካልም ፡ የመንፈስም ፡ ብርታት ፡ ጐልቶ ፡ ይታይባቸው ፡ ነበር ። ይኸንኑ ፡ የተገነዘቡት ፡ አያታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ በላይነሽ ፡ ረዴ ፥ "ማንኩልኽ" ፡ አሏቸው ።

ልጅ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ አብዛኛውን ፡ የሕፃንነትና ፡ የልጅነት ፡ ዘመናቸውን ፡ ይፋት ፡ (መንግሥት ፥ ጎራት ፥ ዐማች ፡ ዐምባ ፥ ቊጣጭ ፡ ዐምባ ፥ ቆቦ) ፡ አሳለፉ ።

## 2

## ትምህርት

በጥንታዊው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልማድ ፥ አራት ፡ ዓመት ፡ ካራት ፡ ቀን ፡ ሲሞላቸው ፥ ደብተራ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንድ ፥ ቀጥሎም ፡ አጎታቸው ፡ አለቃ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንድ ፥ እንዲሁም ፡ መምህር ፡ ተቀጥረውላቸው ፥ ከፊደል ፡ መቊጠር ፡ እስከ ፡ ዳዊት ፡ መድገም ፡ ያለውን ፡ ባህላዊ ፡ የቀለም ፡ ትምህርት ፡ ባስደናቂ ፡ ፍጥነት ፡ አጠናቀቁ ። በጊዜው ፡ ለጨዋ ፡ ልጅ ፡ ኹሉ ፡ ይሰጥ ፡ የነበረውንም ፡ የሥርዐት ፥ የጠመንጃ ፡ ተኵስ ፥ የውሃ ፡ ዋና ፥ የፈረስ ፡ ግልቢያና ፡ የመሳሰለውን ፡ ትምህርት ፡ አገኙ ።

ልጅ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሞላ ፥ በ 30 ፡ ዓመታቸው ፡ ባረፉ ፡ ባመቱ ፥ ባ 1917 ፡ ዓ.ም. ፥

ልጅ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ከወንድሞቻቸው ፡ ከልጅ ፡ አሰፋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴና ፡ ከልጅ ፡ ለማ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፥ እናታቸውን ፡ ወይዘሮ ፡ ደስታ ፡ አባዬን ፡ ተከትለው ፥ ያባታቸውን ፡ የወግ ፡ ዕቃ ፡ ለመንግሥት ፡ ለማግባት ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ዘንድ ፡ ቀረቡ ። ልጅ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንንን ፡ በዚህ ፡ ዕለት ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ አዩአቸው ፤ ስላባታቸውም ፡ ማረፍ ፡ የገለጹላቸው ፡ የሐዘን ፡ ስሜትና ፡ የማጽናናት ፡ ቃል ፡ በልጅነት ፡ አእምሯቸው ፡ ለመቼውም ፡ ተቀርጾ ፡ ኖረ ።

ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፦ *የልጅ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፡ ልጆች ፡ ማስተማር ፡ የኛ ፡ ተግባር ፡ ነው ፡* ቢሉም ፥ የልጆቹ ፡ ዕድሜ ፡ ማነስ ፡ ከቤተሰብ ፡ ርቆ ፡ ለመኖር ፡ ስላልፈቀደ ፥ ከኹለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፡ ከይፋት ፡ ይዘዋቸው ፡ እንዲመጡ ፡ ወይዘሮ ፡ ደስታን ፡ ዐደራ ፡ አሉ ።

በዚሁ ፡ ሰሞን ፥ ወንድሞቻቸው ፥ ልጅ ፡ አሰፋና ፡ ልጅ ፡ ለማ ፥ ዕድሜያቸው ፡ ሰባት ፡ ዓመትን ፡ ስላለፈ ፥ ብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ ዘንድ ፡ ቀርበው ፡ ዲቁናቸውን ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ -- ልጅ ፡ መኾን ፡ አይቀርም -- ታናሽ ፡ ወንድማቸውን ፡ ናቅ ፡ ቢያደርጓቸው ፥ *"ማን ፡ እኩል ፡ ኽ"* ፡ በነገሩ ፡ ተነክተው ፥ የምር ፡ እያለቀሱ ፦ *እኔም ፡ ዲቁና ፡ ልቀበል* ፥ ብለው ፡ እናታቸውን ፡ ጧት ፡ ማታ ፡ አስቸገሯቸው ። ወይዘሮ ፡ ደስታም ፥ የብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ ጸሓፊ ፡ የኾኑ ፡ ሰውን ፡ አማላጅ ፡ እንዲኾኗቸው ፡ ለምነው ፥ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ እብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ማርቆስ ፡ ዘንድ ፡ ቀርበውና ፥ ተፈላጊውን ፡ የቃል ፡ ጥናት ፡ ጥያቄ ፡ አለስሕተት ፡ መልሰው ፥ በስድስት ፡ ዓመታቸው ፡ ዲቁናቸውን ፥ እንደ ፡ ወንድሞቻቸው ፥ ተቀብለው ፡ ምስጢር ፡ ለማየት ፡ በቁ ።

ይፋት ፡ ተመልሰው ፥ ኹለት ፡ ዓመት ፡ እንደ ፡ ሞላም ፥ ባ 1919 ፡ ዓ.ም. ፥ የልጅ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማኅበርተኞች ፥ እነደጃዝማች ፡ አበበ ፡ አውራሪስ ፥ ልጅ ፡ (ኋላ ፥ ቢትወደድ) ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፥ ልጅ ፡ መኰሪያ ፡ ይገባሻል ፥ ባላምባራስ ፡ (ኋላ ፥ ራስ) ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፥ ነጋድራስ ፡ አበበ ፡ ድረስ ፥ ልጅ ፡ ኀይለ ፡ ማርያም ፡ ገዝሙ ፡ አንድ ጋ ፡ ኾነው ፥ *"ዐልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ባዘዙት ፡ መሠረት ፥ ልጆችዎ ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ እንዲገቡ ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ይላኳቸው"* ፡ የሚል ፡ ማስታወሻ ፡ ደብዳቤ ፡ ለወይዘሮ ፡ ደስታ ፡ ጻፉላቸው ።

ከጥቂት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፥ ሦስቱ ፡ ወንድማማቾች ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ እንደ ፡ መጡ ፥ ካባታቸው ፡ ማደሪያ ፡ በደጃዝማች ፡ ይገዙ ፡ በሀብቴ ፡ በኩል ፡ እየተሰበሰበ ፥ በወር ፡ 30 ፡ ብር ፡ እንዲከፈልላቸው ፡ ኾኖ ፥ እተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ባዳሪነት ፡ ተመዝግበው ፥ ዘመናዊ ፡ ትምህርታቸውን ፡ በፈረንሳዊ ፡ ቋንቋ ፡ ለሰባት ፡ ዓመት ፡ ተከታተሉ ።




*(ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ)* ፤ ልጅ ፡ ነጋ ፥ ልጅ ፡ አሰፋ ፥ ልጅ ፡ ለማ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥
ዐዲስ ፡ አበባ ፥ እተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ተማሪዎች ፡ ኾነው ።

ሦስቱም ፡ ልጆች ፡ እጅግ ፡ ብሩህ ፡ አእምሮ ፡ ነበራቸውና ፥ በመዠመሪያው ፡ ዓመት ፥ ያንደኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርታቸውን ፡ ባስደናቂ ፡ ውጤት ፡ አጠናቀው ፥ ባምስተኛው ፡ ዓመት ፡ ልጅ ፡ አሰፋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ በሰባተኛው ፡ ዓመት ፡ ደግሞ ፥ ልጅ ፡ ለማና ፡ ልጅ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ መፈጸሚያና ፡ የዩኒቨርሲቲ ፡ መግቢያ ፡ *"ባካሎሬያ ፡ ሲያንቲፊክ"* ፡ ፈተናቸውን ፥ ባ 1924 ና ፡ ባ 1926 ፡ ዓ.ም. ፡ መጨረሻ ፥ በ *"ፍጹም ፡ ጥሩ"* ፡ *("ኤክሰለንት")*ና ፡ በ *"እጅግ ፡ ጥሩ"* ፡ *("ትሬ ፡ ቢየን")* ፡ ማዕርግ ፡ ዐልፈዋል ። ይኸውም ፡ የባካሎሬያ ፡ ፈተና ፡ በኢትዮጵያ ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መካኼዱ ፡ ነበር ። በዚሁ ፡ ብልኅነታቸው ፥ እንዲሁም ፡ በትሕትናቸውና ፥ በግብረ ፡ ገብነታቸው ፥ አስተማሪዎቻቸውም ፡ ኾኑ ፡ የተማሪ ፡ ቤት ፡ ጓደኞቻቸው ፡ በተለይ ፡ ወደዷቸው ፥ አከበሯቸው ፥ ተመኩባቸው ፤ *"የተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ኮከቦች"* ፡ የሚል ፡ ማቈላመጫ ፡ ስምም ፡ አወጡላቸው ።

ልጅ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ በሒሳብ ፥ በሳይንስ ፥ በሥዕልና ፡ በሙዚቃ ፡ የተለየ ፡ ስጦታ ፡ ነበራቸው ፤ ባዲስ ፡ አበባ ፡ ትምህርት ፡ ቤቶችም ፡ መኻከል ፡ በተደረጉ ፡ የሙዚቃም ፡ የሥዕልም ፡ ውድድሮች ፥ አንደኛ ፡ እየወጡ ፥ ከንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ እጅ ፡ ሽልማትን ፡ ተቀብለዋል ።

ባካሎሬያቸውን ፡ አግኝተው ፥ ለከፍተኛ ፡ ትምህርት ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ እንዲኼዱ ፡ መወሰኑ ፡ ሲነገራቸው ፥ *"ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመውረር ፡ እየተሰናዳች ፥ አገሬን ፡ ጥዬ ፡ አልኼድም"* ፡ ብለው ፥ ወደጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ለመግባት ፡ ያላቸውን ፡ ፍላጎት ፡ ገለጹ ። እጦር ፡ ትምህርት ፡ ለመግባት ፡ የዕድሜያቸው ፡ ማነስ ፡ እንደማይፈቅድላቸው ፡ ቢነገራቸው ፥ ለግርማዊነታቸው ፡ አመልክተው ፥ ከስድስት ፡ ወር ፡ ጥበቃ ፡ በኋላ ፥ በልዩ ፡ ፈቃድ ፥ በጥር ፡ ወር ፡ 1927 ፡ ዓ.ም. ፡ እገነት ፡ ሆሎታ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ገብተው ፥ ከትምህርቱ ፡ ተሳተፉ ።



(ከግራ ፡ በኩል) ፥ ዕጩ ፡ መኰንን ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ የመድፈኝነት ፡ ትምህርት ፡ ሲከታተሉ ፤ ገነት ፡ ሆሎታ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፥ 1927 ፡ ዓ.ም. ።



ሊ.. ፡ ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ያዲሱ ፡ ብሪጋድ ፡ ኤታ ፡ ማገሮር ፡ ሹም ፡ ተብለው ፡ እንደ ፡ ተሠየሙ ፤
ገነት ፥ የካቲት ፡ 21 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ።

በስዊድን ፡ ወታደራዊ ፡ ተልእኮ ፡ በፈረንሳዊ ፡ ቋንቋ ፡ የተሰጠው ፡ የጦር ፡ ትምህርት ፡ ሙሉ ፡ በሙሉ ፡ የፈረንሳ ፡ ጦር ፡ አካዴሚ ፡ ትምህርት ፡ መርሐ ፡ ግብር ፡ ነው ። ወቅቱ ፡ አስቸኳይ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ የሦስቱን ፡ ዓመት ፡ የጦር ፡ ትምህርት ፡ መርሐ ፡ ግብር ፥ ዓመት ፡ ተመንፈቅ ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፥ አንደኛ ፡ በመውጣት ፡ አጠናቀው ፥ በመድፈኛ ፡ ደንብ ፡ ውስጥ ፥

- *ኅዳር* ፡ 14 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፥ *የመቶ ፡ አለቃ* ፤
- *ታኅሣሥ* ፡ 14 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፥ *የሻምበል* ፤
- ጥር ፡ 21 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፥ *የሻለቃ* ፡ (ያ 5 ፡ ሻምበል ፡ አዛዥ) ፤
- በመጨረሻም ፥ የካቲት ፡ 21 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፥ *በሌ.የተና ፡ ኮሎኔልነት* ፡

*ማዕርግ* ፥ *ዐዲስ* ፡ ለተቋቋመው ፡ ብሪጋድ ፡ *ዋና ፡ ኤታ ፡ ማገሮር ፡ ሹም* ፡ ኾነው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተሠየሙ ።

## 3
## አገልግሎት

ወዲያው ፥ ሚያዝያ ፡ 13 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፥ ዐዲሱን ፡ ጦር ፡ በኤታ ፡ ማገሮር ፡ ሹምነት ፡ በጣርማ ፡ በር ፡ ግንባር ፡ አዘመቱ ።

የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ከተፈታ ፡ በኋላ ፥ ጥቂት ፡ የገነት ፡ መኰንኖችንና ፡ ጭፍሮችን ፡ ይዘው ፥ ሚያዝያ ፡ 24 ፡ ቀን ፡ 1928 ፡ ዓ.ም. ፡ ዐርበኝነት ፡ ወጡ ።

እስካ 1930 ፡ ዓ.ም. ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፥ ለኹለት ፡ ዓመት ፡ ተኩል ፥

- *ሸዋ* ፡ (ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ዙሪያ ፥ ሙሎ ፥ ሰላሌ ፥ ተጕለት ፥ መርሐቤቴ ፥ ግንደበረት ፥ ጊዳ ፥ ሜጫ ፥ ሜታ ፥ ...) ፤
- *ወሊጋ* ፡ (አሞሩ ፥ ኤበንቱ ፥ ጨልያ ፥ ሆሮ ፥ ጉድሩ ፥ ...) ፥
- *ጎጃም* ፡ (አለፋ ፡ ጣቁሳ ፥ ቡሬ ፥ አሰዋ ፡ ጉደራ ፥ አገው ፡ ምድር ፥ ማቻከል ፥ ...) ፥

ከደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋው ፡ ዳርጌ ፥ ከራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይና ፥ ከታላላቅ ፡ ያርበኝነት ፡

መሪዎች ፡ ጋራ ፡ በጦር ፡ መሪነት ፥ እዚህ ፡ ሊዘረዘሩ ፡ በማይችሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውጊያዎች ፡ በታላቅ ፡ ዠግንነት ፡ ተዋግተውና ፡ አዋግተው ፥ ባርበኞች ፡ ዘንድ ፡ የላቀ ፡ ዝናን ፥ የተለየ ፡ አድናቆትን ፡ አትርፈዋል ።

ዕለት ፡ በለት ፡ ከሚገጥማቸው ፡ የሞት ፡ አደጋ ፡ ሌላ ፥ የዘወትሩ ፡ እንግልት ፡ እንግልት ፡ ሳይመስላቸው ፥ እንዲሁም ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ ሽው ፡ የሚለው ፡ እንደ ፡ ተስቦና ፡ ወባ ፡ ያለ ፡ በሽታ ፥ አንዱም ፡ ሳይበግራቸው ፥ ኹለት ፡ ዓመት ፡ ያኽል ፡ እንደ ፡ ተዋጉ ፥ ጎጃም ፡ ላይ ፡ ኾነው ፡ በተደረገው ፡ ያርበኞች ፡ ጉባኤ ፥ ባርበኝነት ፡ መሪዎች ፡ መኻከል ፡ የጦር ፡ ዐቅድ ፡ ልዩነት ፡ ተፈጥሮ ፥ የተወሰኑ ፡ መሪዎች ፥ *"መደባችንን ፡ እሱዳን ፡ ጠረፍ ፡ ላይ ፡ አድርገን ፥ ትግላችንን ፡ እንቀጥል"* ፡ ሲሉ ፥ ሌ. ፡ ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ደግሞ ፥ *"ወደ ፡ ሽዋ ፡ ተሻግረን ፥ እመኻል ፡ ኢትዮጵያ ፡ ውጊያውን ፡ እንቀጥል"* ፡ የሚለውን ፡ ቍርጠኛ ፡ ዐቅድ ፡ በመግለጽ ፥ ያመዛኙን ፡ ዐርበኛ ፡ ድጋፍ ፡ አግኝተው ፥ ከደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋውና ፡ ካብዛኛው ፡ ጦር ፡ ጋራ ፥ ወደ ፡ ሽዋ ፡ መንገድ ፡ ዠመሩ ። ዐባይ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ደረሱም ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ በተረዳ ፡ ኹኔታ ፡ ባልታወቃቸው ፡ ምክንያት ፥ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ 1930 ፡ ዓ.ም. ፥ በደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አሰፋው ፡ ዳርጌ ፡ አሳሳቢነት ፥ መኳንንቱ ፡ መክረው ፥ ሌ. ፡ ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይል ፡ ሥላሴ ፡ በወቅቱ ፡ እታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ በስደት ፡ ለሚገኙት ፡ ለግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዐፄ ፡ ኀይል ፡ ሥላሴ ፡ መልክት ፡ እንዲያደርሱላቸው ፡ ጠየቋቸው ። የመልክቱ ፡ ዓላማ ፥ ያርበኝነት ፡ ተጋድሎው ፡ የደረሰበትን ፡ ደረጃ ፥ ያስገኛቸውንም ፡ ውጤቶች ፡ አስታውቆና ፥ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ ግንኙነትን ፡ መሥርቶ ፥ የጦር ፡ መሣሪያና ፡ የሥንቅ ፡ ርዳታ ፡ በቶሎ ፡ ላርበኛው ፡ እንዲደርስ ፡ ለማስደረግ ፡ ነበር ። ሌላው ፡ ምክንያት ፡ ደግሞ ፥ ደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋው ፥ የራስ ፡ ዳርጌ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ በመኾናቸው ፥ *"ሊነግሡ ፡ ነው"* ፡ የሚል ፡ ዐሚታ ፡ ይሰማባቸው ፡ ነበርና ፥ ይኽንን ፡ መሠረተ ፡ ቢስ ፡ ወሬ ፡ ለማስተባበል ፡ ያደረጉት ፡ መስሎ ፡ ነበር ። ሌ. ፡ ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይል ፡ ሥላሴ *፦ በምትኬ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ይላክ ፤ እኔ ፡ ውጊያውን ፡ ትቼ ፡ ልኼድ ፡ አልችልም ፤* የሚል ፡ መልስ ፡ ቢሰጡም ፥ ደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋው ፡ ድንጋይ ፡ ተሸክመው ፡ ስለ ፡ ለምኗቸው ፥ ሳይወዱ ፡ በግዴታ ፡ መልክተኝነቱን ፡ ተቀብለው ፥ ወንበርማ ፥ ሚያዝያ ፡ 28 ፡ ቀን ፡ 1930 ፡ ዓ.ም. ፡ የተጻፈውን ፡ ደብዳቤ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ለማድረስ ፥ ከሻምበል ፡ እንግዳ ፡ ወልደ ፡ ማርያምና ፡ ከጥቂት ፡ ዐርበኞች ፡ ጋራ ፥ ነሐሴ ፡ 4 ፡ ቀን ፡ 1930 ፡ ዓ.ም. ፡ ወደ ፡ ሱዳን ፡ ጕዞ ፡ ዠመሩ ።

በወቅቱ ፥ ሱዳንን ፡ በቅኝ ፡ ግዛትነት ፡ ይገዛ ፡ የነበረው ፡ የታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ መንግሥት ፥ ኢትዮጵያን ፡ ለኢጣሊያ ፡ ዐውቆ ፡ ኖሮ ፥ መስከረም ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 1931 ፡ ዓ.ም. ፥ ሌ. ፡ ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይል ፡ ሥላሴ ፡ ከተከተሏቸው ፡ ዐርበኞች ፡ ጋራ ፥ የሱዳንን ፡ ጠረፍ ፡ እንዳለፉ ፥ ጠረፉን ፡ የሚጠብቀው ፡ የብሪታንያ ፡ ጦር ፡ ይይዛቸዋል ። ጥቂት ፡ ወራት ፡ በጦር ፡ እስረኝነት ፡ ገዳሬፍና ፡ ካርቱም ፡ እንደ ፡ ቈዩ ፥ ኢጣልያ ፡ በታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ ላይ ፡ ጦርነት ፡ በማወጇ ፥ የታሰሩት ፡ ዐርበኞች ፡ ተፈቱ ። ሌ. ፡ ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይል ፡ ሥላሴም ፥ የተላኩለትን ፡ መልክት ፡ በብሪታንያ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ በኩል ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አስተላልፈው ፥ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ለመመለስ ፥ ዐብረዋቸው ፡ የሚዘምቱ ፡ ኹለት ፡


ሺሕ ፡ የሚኾኑ ፡ ስደተኞችን ፡ ላርበኝነት ፡ አሰባስበው ፡ በሚያደራጁበት ፡ ጊዜ ፥ የታላቋ ፡ ብሪታንያ ፡ መንግሥት ፡ በጎ ፡ ፈቃድና ፡ ወታደራዊ ፡ ድጋፍ ፡ ደረሰላቸው ።



ደጃዝማች ፡ ዘውዴ ፡ አስፋው ፡ ዳርጌ ።



ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ።



ሊ. ፡ ኰሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ 1933 ፡ ዓ.ም. ።

ሠኔ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 1932 ፡ ዓ.ም. ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ከብሪታንያ ፡ ወደ ፡ ካርቱም ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፥ ሊ. ፡ ኰሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፡ አስጠርተው ፥ ሶባ ፡ እተባለው ፡ የሱዳን ፡ ቀበሌ ፥ ዐዲስ ፡ የሚቋቋመውን ፡ ቅዱስ ፡ ጊዮርጊስ ፡ የጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ከብሪታንያ ፡ ጦር ፡ መኰንኖች ፡ ጋራ ፡ በጣምራ ፡ እንዲመሩ ፡ አዘዟቸው ።

በወቅቱ ፡ የመርድ ፡ አዝማች ፡ አስፋ ፡ ወሰን ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወታደራዊ ፡ ማዕርግ ፡ የሻለቃ ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ከርሳቸው ፡ ማዕርግ ፡ በልጦ ፡ እንዳይገኝ ፥ ሊ. ፡ ኰሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ማዕርጋቸው ፡ አንድ ፡ ደረጃ ፡ ዝቅ ፡ ብሎ ፥ በሻለቅነት ፡ ማዕርግ ፡ ሥራቸውን ፡ እንዲቀጥሉ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ታዘዙ ፤ ኰሎኔሉም *፦ ጃንሆይ ፤ ጕዳዬ ፡ ከሥራው ፡ እንጂ ፡ ከማዕርጉ ፡ አይደለም ፤* ብለው ፡ ተቀበሉ ።

ከስድስት ፡ ወር ፡ ዝግጅት ፡ በኋላ ፥ የካቲት ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ ኢትዮጵያ ፡ ገብተው ፥ ከ 3 ፡ ወር ፡ ዘመቻ ፡ በኋላ ፥ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከኢጣሊያ ፡ ጦር ፡ እጅ ፡ ነጻ ፡ ወጣች ። ሻለቃ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ በጦሩ ፡ በኩል ፡ ለሚኖረው ፡ ጉዳይ ፡ ኹሉ ፡ ኀላፊ ፡ ኾነው ፥ የንጉሠ ፡ ነገሥቱንም ፡ ወታደራዊ ፡ መመሪያ ፡ ይዘው ፥ ከምክትሎቻቸው ፡ ከሻለቃ ፡ ዐቢይ ፡ አበበና ፡ ከሻለቃ ፡ ሙሉጌታ ፡ ቡሊ ፡ ጋራ ፥ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸውን ፡ ዐጅበው ፥ ሚያዝያ ፡ 5 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ በማለዳ ፡ ከደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ባየርዠበብ ፡ (አይሮፕላን) ፡ ተጉዘው ፥ ኢትዮጵያ ፡ መናገሻ ፡ ከተማ ፥ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ ጧቱኑ ፡ ገቡ ።

ሻለቃ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፡ ካርበኝነት ፡ ዘመን ፡ አንሥቶ ፡ ያውቋቸውና ፡ ያደንቋቸው ፡ የነበሩት ፥ ዝነኛዋ ፡ ባለቅኔ ፡ ንጋቷ ፡ ከልካይ ፥ የምሥራቹን ፡ እንደ ፡ ሰሙ ፥

*ጠቅል ፡ ባንዲራውን ፡ ጠረፍ ፡ ቢዘረጋ ፥*
*ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ አስቀድሞ ፡ ነጋ ።*

ሲሉ ፡ ገጠሙላቸው ።

ዐዲስ ፡ አበባ ፡ እንደ ፡ ገቡም ፥ ጽሕፈት ፡ ቤታቸውን ፡ በጃንሆይ ፡ ዐፄ ፡ ምኒልክ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ አድርገው ፥ ያርበኛውን ፡ ጦር ፡ በከተማዋ ፡ ዙሪያ ፡ አዋቅሮ ፡ በማስምራትና ፥ ከብሪታንያ ፡ ጦር ፡ ኀላፊዎች ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ በመሥራት ፥ የከተማውን ፡ ጠቅላላ ፡ ጸጥታ ፡ አረጋግጠው ፥ ወታደራዊ ፡ አስተዳደሩን ፡ አደራጅተው ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥታቸውን ፡ በመናገሻ ፡ ከተማዋ ፡ ለመቀበል ፡ አስፈላጊውን ፡ ዝግጅትና ፡ መስተንግዶ ፡ አከናወኑ ። በዚህ ፡ ሥራቸው ፥ ከብሪታንያ ፡ ጦር ፡ አመራር ፡ ጋራ ፥ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፥ አለመግባባትና ፡ ግጭት ፡ ቢፈጠርም ፡ ቅሉ ፥ ሻለቃ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ አንዳችም ፡ ጊዜ ፡ ቢኾን ፡ የኢትዮጵያን ፡ እግዚእና ፡ ሳያስደፍሩ ፥ ክብሯንም ፡ ሳያስነኩ ፥ ተልእኳቸውን ፡ ጠንቅቀው ፡ ፈጽመዋል ።



ያዲስ ፡ ዓለም ፡ ምሽግ ፡ እንደ ፡ ተሰበረ ።
*(ግራ ፡ ጽንፍ)* ፤ ወይዘሮ ፡ ሸዋረገድ ፡ ገድሌ ፥
*(መኻል)* ፤ ሻለቃ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፤
*(ቀኝ ፡ ጽንፍ)* ፤ የብሪታንያ ፡ ጦር ፡ አዛዥ ፡ ጀኔራል ፡ ካኒንግሀም ።

ሚያዝያ ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፥ በድል ፡ አድራጊነት ፥ መናገሻ ፡ ከተማቸው ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ እንደ ፡ ገቡ ፥ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ የመቈጣጠርና ፡ ኹለተኛውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥታዊ ፡ መንግሥት ፡ የመመሥረቱ ፡ ዐቢይ ፡ ሥራ ፡ ተዠመረ ። ኾኖም ፥ የብሪታንያ ፡ ጦር ፡ አለቆች ፥ ኢትዮጵያን ፡ በቅኚነት ፡ እንጂ ፡ በሐራ ፡ መንግሥትነት ፡ ዳግመኛ ፡ ለማየት ፡ አይፈልጉም ፡ ነበርና ፥ ዐዲስ ፡ መንግሥት ፡ የማቆሙን ፡ ሐሳብ ፡ አጥብቀው ፡ እንደሚቃወሙ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አስታወቋቸው ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፥ የእንግሊዞቹን ፡ ተቃውሞ ፡ ጥሰው ፥ ግንቦት ፡ 2 ፡ ቀን ፡ 1933 ፡ ዓ.ም. ፥ ሰባት ፡ ሚኒስትሮችን ፡ በመሾም ፥ ዐዲሱን ፡ መንግሥታቸውን ፡ አቋቋሙ ፤ ሻለቃ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴንም ፥ በኻያ ፡ ሦስት ፡ ዓመታቸው ፥ ከበላይ ፡ ሚኒስትር ፡ ሳይኖርባቸው ፥ የጦር ፡ ሚኒስቴር ፡ ዋና ፡ ጸሓፊ ፡ ብለው ፡ ሾሟቸው ። በዚህ ፡ ኀላፊነታቸው ፥ ጦራዊ ፡ አስተዳደሩን ፡ በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዘረጉ ፥ ዘመናዊውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ጦር ፡ ሰራዊትም ፡ ወጠኑ ።

ባ 1934 ፡ ዓ.ም ፥ ጦራዊው ፡ አስተዳደር ፡ አብቅቶ ፡ ሲቪሉ ፡ መንግሥት ፡ ሲቋቋም ፡ በተደረገው ፡ ሹምሽር ፥ ታላቁ ፡ ዐርበኛና ፡ ሀገራዊው ፡ ዠግና ፥ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትር ፡ ኾነው ፡ ሲሾሙ ፥ ሻለቃ ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ በዚያው ፡ በጦር ፡ ሚኒስቴር ፡ ዋና ፡ ጸሓፊነታቸው ፡ ቀጠሉ ። ይህ ፡ ከባድ ፡ ኀላፊነት ፡ ባስከተለባቸው ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ የሥራ ፡ ድርሻ ፥ አላንዳች ፡ ዕረፍት ፥ ከኹለት ፡ ዓመት ፡ በላይ ፡ ተጠምደው ፡ በመሥራታቸው ፥ መላ ፡ አካላቸው ፡ ጥኑ ፡ ጕዳት ፡ አገኘው ፤ ዐይኖቻቸውም ፡ ፈጽሞ ፡ እመታወር ፡ ደረጃ ፡ ደረሱ ።

መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 1936 ፡ ዓ.ም. ፥ በኮሎኔልነት ፡ ማዕርግ ፥ የሕዝብ ፡ ጸጥታ ፡ ዋና ፡ ዲሬክተር ፡ ተብለው ፡ ተሾሙ ። የጸጥታ ፡ ሹምነቱ ፡ የማይኾንላቸው ፡ መኾኑን ፡ ገልጠው ፡ ቢከላከሉም ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አጸኑባቸው ። ኾኖም ፥ በጤና ፡ ምክንያት ፡ ኀላፊነታቸውን ፡ በሚገባ ፡ መወጣት ፡ ስላልቻሉ ፥ ከጥቂት ፡ ወራት ፡ ያልተሟላ ፡ አገልግሎት ፡ በኋላ ፥ ከሥራው ፡ ተሰናብተው ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፈቃድ ፥ ለሕክምና ፡ ወደ ፡ ካይሮ ፡ ኼዱ ።

ከዘጠኝ ፡ ወር ፡ ሕክምና ፡ በኋላ ፥ ፈጽመው ፡ ድነው ፥ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንደ ፡ ተመለሱ ፥ ጥቅምት ፡ 15 ፡ ቀን ፡ 1938 ፡ ዓ.ም. ፥ *አስመራ ፥ የኢትዮጵያ ፡ አገናኝ ፡ መኰንን ፡* ተብለው ፡ ተሾሙ ፤ በጦር ፡ ሚኒስቴር ፡ ያፈሯቸውም ፡ ምርጥ ፡ የሥራ ፡ ባልደረቦቻቸው ፡ በየኀላፊነቱ ፡ ተበታተኑ ። ምንም ፡ ሹመቱ ፡ የግዞት ፡ መልክ ፡ ቢይዝ ፥ አገርን ፡ ማገልገል ፡ ከምንም ፡ ምን ፡ አብልጠው ፡ የሚወዱት ፡ ተግባር ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፥ በኢጣሊያ ፡ ቅኝ ፡ ገዦች ፡ ግፍ ፥ ከኢትዮጵያ ፡ የተገነጠለችውን ፡ መረብ ፡ ምላሽ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወደ ፡ እናት ፡ አገሯ ፡ መመለስ ፥ ከልጅነታቸው ፡ አንሥቶ ፥ እግዚአብሔርን ፡ የሚለምኑት ፡ ምኞታቸው ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ሹመቱን ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉ ። እጦር ፡ ሚኒስቴር ፡ ጸሓፊያቸው ፡ የነበሩትንና ፥ በችሎታቸው ፡ የሚያደንቋቸውን ፡ አቶ ፡ ተኮላ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ አኹንም ፡ ጸሓፊያቸው ፡ አድርገው ፥ መጋቢት ፡ 12 ፡ ቀን ፡ 1938 ፡ ዓ.ም. ፡ አስመራ ፡ ገቡ ።




ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥
አስመራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ አገናኝ ፡ መኰንን ፥ ሥራቸውን ፡ እንደ ፡ ዠመሩ ፤ መጋቢት ፡ 1938 ፡ ዓ.ም. ።

ምንም ፡ ሥራቸው ፡ በቆንስል ፡ ደረጃ ፡ ቢኾን ፥ ከቆንስልነት ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚገኘው ፡ መባሕታዊ ፡ ምጉብነት ፡ ወይም ፡ *"ዲፕሎማቲክ ፡ ኢምዩኒቲ"* ፡ ለርሳቸው ፡ አልተሰጠም ፤ እንዲያውም ፥ የሥልጣን ፡ ደብዳቤያቸው ፡ *"አንዳች ፡ ወንጀል ፡ ፈጽመው ፡ ቢገኙ ፥ ባገሩ ፡ ሕግና ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ይቀጣሉ"* ፡ የሚል ፡ ቃል ፡ ሰፍሮበታል ። ለመዠመሪያዎቹ ፡ ዓመታትም ፥ ለሠራተኛ ፡ ደሞዝ ፥ ለቤት ፡ ኪራይና ፡ ለመሳሰለው ፡ ወጪ ፡ ካልኾነ ፡ በቀር ፥ የፖለቲካ ፡ ሥራን ፡ የሚያሠራ ፡ ባጀት ፡ ከመንግሥት ፡ አልተመደበላቸውም ።

አስመራም ፡ እንደ ፡ ገቡ ፥ መኪናቸው ፡ ላይ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰንደቅ ፡ ዓላማ ፡ እያውለበለቡ ፥ በያውራጃው ፡ እየተዘዋወሩ ፥ ከመኳንንቱም ፥ ከሕዝቡም ፡ ጋራ ፡ ሲነጋገሩ ፥ እስላም ፡ ክርስቲያን ፡ ሳይል ፥ እኹሉም ፡ ዘንድ ፡ እኩል ፡ የጋለ ፡ ኢትዮጵያንና ፡ ኢትዮጵያዊነትን ፡ የማፍቀር ፡ ስሜት ፥ ከፈረንጅ ፡ ባርነት ፡ ቀንበርም ፡ ነጻ ፡ ወጥቶ ፥ ከናት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ዳግመኛ ፡ የመወሐድ ፡ ጽኑ ፡ ፍላጎት ፥ ከጠበቁት ፡ የበለጠ ፡ ርግጥ ፡ ኾኖ ፡ አገኙት ። ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴም ፥ ምንም ፡ ተልእኳቸው ፡ በቂ ፡ የሥራ ፡ ነጻነት ፡ ባይሰጣቸው ፥ የኤርትራ ፡ ጉዳይ ፡ የሚዠመረውም ፥ ደኀኛ ፡ ፍጻሜ ፡ የሚያገኘውም ፡ በፍቅርና ፡ በፍቅር ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ በጥልቅ ፡ ስለ ፡ ተረዱት ፥ ከግራና ፡ ከቀኝ ፡ ለሚደቀንበት ፡ የጥቃትና ፡ የትንኰሳ ፡ ተንኰል ፥ ሕዝቡ ፡ ትግሥትንና ፡ ሰላምን ፡ እንዲያሳይ ፥ ርስ ፡ በርሱም ፡ ፍቅርን ፡ እንዲያዳብር ፡ መከሩ ። ባሠራር ፡ ረገድ ፡ ደግሞ ፥ የኤርትራ ፡ ነዋሪ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ የመቀላቀል ፡ የተቀደሰ ፡ ዓላማውን ፡ እዳር ፡ ለማድረስ ፡ ባቋቋመው ፡ *"የኢትዮጵያና ፡ ኤርትራ ፡ አንድነት ፡ ማኅበር ፥ አንዲት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ ሞት"* ፡ በተሠኘው ፡ አንድነቱ ፡ አካል ፡ ሠርቶ ፡ ሲታገል ፥ የማኅበሩ ፡ መሪ ፡ አካል ፥ የወከለውን ፡ ሕዝብ ፡ ሳያማክር ፥ ለብቻው ፡ ማንኛውንም ፡ ውሳኔ ፡ የመወሰንም ፡ ኾነ ፡ ውል ፡ የመዋዋል ፡ አሠራር ፡ ነበረው ። ይህም ፡ አሠራር ፡ ለጠላት ፡ ፍንጭን ፡ እየሰጠው ፥ መሪውን ፡ አካል ፡ በመቈጣጠር ፡ ብቻ ፥ ትግሉን ፡ በቀላሉ ፡ እያዳከመውና ፡ እያጨናገፈው ፡ ስላስቸገረ ፥ ለችግሩ ፡ መፍትሔ ፡ ማግኘት ፡ ተገደዱ ።

መፍትሔውም ፥ ያንድነቱን ፡ ሥልጣን ፡ አወቃቀር ፥ ከጭቃ ፡ እስከ ፡ ቀበሌ ፥ ከቀበሌ ፡ እስከ ፡ ምክትል ፡ ወረዳ ፥ ከምክትል ፡ ወረዳ ፡ እስከ ፡ ወረዳ ፥ ከወረዳ ፡ እስካውራጃ ፥ ካውራጃ ፡ እስከ ፡ መላዬቱ ፡ ኤርትራ ፡ አረማምዶ ፡ ማውጣትና ፡ ማውረድ ፡ በሚያስችል ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አወቃቀር ፡ በፍጥነት ፡ እንዲዋቀር ፡ አስደረጉ ። ባዲሱ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አወቃቀርም ፡ መሠረት ፥ አጠቃላይ ፡ ምርጫ ፡ ተደርጎ ፥ በችሎታም ፡ በታማኝነትም ፡ ልቀው ፡ የተመረጡት ፡ የሕዝብ ፡ እንደራሴዎች ፥ ከወከላቸው ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ እንዳንድ ፡ ልብ ፡ መካሪ ፥ እንዳንድ ፡ ቃል ፡ ተናጋሪ ፡ ኾነው ፥ በሙሉ ፡ ችሎት ፡ ሥራቸውን ፡ ተያያዙት ፤ ሕዝቡንም ፥ በሚያገምረው ፡ ግሥጋሤ ፡ መርተው ፥ እተመኘው ፡ ፍጻሜ ፥ እባሕርያዊ ፡ አንድነቱ ፡ በሰላም ፡ አደረሱት ።



ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ከኢትዮጵያና ፡ ኤርትራ ፡ አንድነት ፡ ማኅበር ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ራስ ፡ ኪዳነ ፡ ማርያም ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ ጋራ ፥ ኢትዮጵያና ፡ ኤርትራ ፡ የተወሐዱ ፡ ዕለት ፤ አስመራ ፥ መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 1943 ፡ ዓ.ም. ።

ርግጥ ፡ ነው ፥ ለኤርትራና ፡ ኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡ የሚታገለው ፡ የኤርትራ ፡ ነዋሪ ፥ በዚሁ ፡ አቋሙ ፡ በቅኝ ፡ ገዢ ፡ ኀይሎች ፡ ከሥራው ፡ የመባረር ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ የመታሰርና ፡ የመገደል ፡ አደጋም ፡ ዘወትር ፡ ይገጥመው ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ አገናኝ ፡ መኰንኑ ፥ የኢትዮጵያን ፡ መንግሥት ፡ ግዛታዊም ፡ ኾነ ፡ ንዋያዊ ፡ ድጋፍ ፡ እየጠየቁና ፥ በሙሉም ፡ ባይኾን ፡ በከፊል ፡ እያገኙ ፥ ለዐያሌ ፡ ያንድነት ፡ ታጋዮች ፡ መከታና ፡ ደራሽ ፡ ኾነውላቸው ፡ ነበር ።

በተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ጠቅላላ ፡ ጉባኤ ፡ ውሳኔ ፡ መሠረት ፥ መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 1943 ፡ ዓ.ም. ፥ ኤርትራ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ጋራ ፡ ለመቀላቀል ፡ በቃች ።

ወጣቱ ፡ መኰንን ፥ የኤርትራ ፡ ተልእኳቸውን ፡ በታላቅ ፡ ትጋት ፡ አከናውነዋል ። አርባ ፡ ስምንት ፡ ሰዓት ፡ እንቅልፍ ፡ ባይናቸው ፡ ሳያልፍ ፡ የሚሠሩበት ፡ ጊዜ ፡ ነበር ። ያገናኝ ፡ መኰንኑ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፥ *"ቪላ ፡ ቪክቶሪያ"* ፥ ለክርስቲያኑም ፡ ለእስላሙም ፥ ለተዋሕዶውም ፡ ለፕሮቴስታንትና ፡ ካቶሊኩም ፡ እኩል ፡ ቤታቸው ፡ ኾነ ። ባርበኝነት ፡ ዘመን ፡ አይተውት ፡ የነበረውን ፡ እውነተኛ ፡ ፍቅር ፡ የሰፈነበትን ፡ ሕይወት ፥ በኤርትራ ፡ የሥራ ፡ ዘመናቸው ፥ እጅግ ፡ እሚወዱትና ፡ ርሱም ፡ *"ነጋዬ ፥ ነጋዬ ፥ ..."* ፡ እያለ ፡ እየዘፈነ ፡ ፍቅሩን ፡ እሚገልጽላቸው ፡ የኤርትራ ፡

ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ዳግመኛ ፡ አግኝተውታል ።

በኤርትራው ፡ አገልግሎት ፡ ዘመናቸው ፥ ከተጠበቀው ፡ አግጣጫ ፡ የሚወረወረው ፡ ጥቃት ፡ አልበቃ ፡ ብሎ ፥ ካልተጠበቀው ፥ ከራሳቸው ፡ ወገን ፥ ካንዴም ፡ ኹለትና ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ የግድያ ፡ ሙከራ ፡ ተቃጥቶባቸዋል ። በያንዳንዱም ፡ ጊዜ ፥ የተላኩት ፡ ገዳዮች ፡ ተልእኳቸውን ፡ ለመፈጸም ፡ ከቃጡ ፡ በኋላ ፥ በእግዚአብሔር ፡ መካሪነት ፥ የሥራቸውን ፡ ክፋትና ፡ የላኪያቸውን ፡ እኩይነት ፡ እያስተዋሉ ፥ ተጸጽተው ፡ ተመልሰዋል ፥ ወይም ፡ በወጡበት ፡ ቀርተዋል ።

ባርበኝነት ፡ ዘመን ፥ የእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፡ ዘወትር ፡ ዐብሯቸው ፡ እየኾነ ፥ ሺሕ ፡ ጊዜ ፡ እሞት ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፥ ሺሕ ፡ ጊዜም ፡ የተረፉት ፡ መኰንን ፥ አኹን ፥ አገር ፡ አማን ፡ በኾነበት ፥ በሰላሙ ፡ ዘመን ፥ የሞት ፡ አደጋው ፡ ቢከታተላቸው ፥ ታላቅ ፡ ወንድማቸው ፥ ልጅ ፡ አሰፋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ባ 1927 ፡ ዓ.ም. ፥ በተወለዱ ፡ በ 20 ፡ ዓመታቸው ፥ በጠና ፡ ታመው ፥ የትምህርት ፡ ቤቶች ፡ ሥራ ፡ አስኪያጅ ፡ ተብለው ፡ ከሚሠሩበት ፡ ከዲሬዳዋ ፡ የላኩላቸው ፡ የኑዛዜ ፡ ቃል ፡ ድንገት ፡ ታሰባቸው ።

ቃሉም ፥ *"እንሆ ፥ እኔ ፥ በተወለድኹ ፡ በ 20 ፡ ዓመቴ ፡ የምለያችኹ ፥ ያባታችን ፡ የኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሞላን ፡ ስም ፡ የሚያስጠራ ፡ ልጅ ፡ ሳልተው ፡ ነው ፤ እናንተ ፡ ግን ፥ ይኽንን ፡ ሳትፈጽሙት ፡ እንዳትቀሩ"* ፡ የሚል ፡ ያደራ ፡ ቃል ፡ ነበር ።

*"በመዠመሪያ ፡ ጽድቁን ፡ ሹ ፤ ሌላው ፡ ኹሉ ፡ ይጨመርላችኋል"* ፡ ያለ ፡ አምላክ ፥ የልባቸውን ፡ አይቶ ፥ ተረከዝ ፡ እስኪነቃ ፡ ቢኬድ ፡ የማትገኘውን ፡ ወይዘሪት ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፡ በቸርነቱ ፡ ዐደላቸው ። ካስመራ ፡ እንደ ፡ ተመለሱም ፥ ሠኔ ፡ 3 ፡ ቀን ፥ 1943 ፡ ዓ.ም. ፡ ሥርዐተ ፡ ጋብቻቸውን ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ እቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፈጸሙ ።



ወይዘሪት ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴና ፡ ኮሎኔል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ቃል ፡ኪዳን ፡ እንዳሰሩ ፤
ዐዲስ ፡ አበባ ፥ የካቲት ፡ 24 ፡ ቀን ፡ 1943 ፡ ዓ.ም. ።

መጋቢት ፡ 13 ፡ ቀን ፡ 1943 ፡ ዓ.ም. ፥ በብሪጋድዬ ፡ ጄኔራልነት ፡ ማዕርግ ፥ በሐረርጌ ፡

ጠቅላይ ፡ ግዛት ፥ የባሌ ፡ አውራጃ ፡ ገዥ ፡ ተብለው ፡ ተሾሙ ።

ዝነኛዋ ፡ ባለቅኔ ፡ ንጋቷ ፡ ከልካይም ፥ የኤርትራን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ መቀላቀልና ፡ የኮሎኔሉን ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ መመለስ ፥ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ባሌ ፡ መኼድ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፥

*"ምን ፡ ያለ ፡ ዕድል ፡ ነው ፡ ጣት ፡ የተነበዘ ፥*
*ገድ ፡ ካከላፋ ፡ አጣምሮ ፡ የያዘ ፤*
*ይባስ ፡ ፈረስ ፡ ጭኖ ፡ የተቅበዘበዘ ፤*
*በጨለማ ፡ ነጋ ፡ አላባት ፡ ታዘዘ ፤*
*ተግዞ ፡ ድል ፡ መታ ፤ ድል ፡ መቶ ፡ ተጋዘ ። "*

ብለው ፡ ገጥመውላቸዋል ።

ምድረ ፡ ገነት ፡ በመሰለው ፡ በባሌ ፡ ግዛት ፥ በሥራ ፡ የካከመ ፡ ሰውነታቸውን ፡ በሚወዱት ፡ የፈረስ ፡ ግልቢያና ፡ ያገር ፡ ጕብኝት ፡ ጠግነው ፥ ባውራጃው ፡ ይታይ ፡ የነበረውን ፡ ለብዙ ፡ ዘመን ፡ የተከማቸ ፡ የሥራ ፡ ውዝፍ ፡ ባጪር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ በዘዴ ፡ ለመቅረፍ ፡ ወሰኑ ። በዚሁ ፡ መሠረት ፥ ምንም ፡ በኀላፊነት ፡ የቈዩበት ፡ ዘመን ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ብቻ ፡ ቢኾን ፥ የባሌ ፡ አውራጃን ፡ ሕዝብ ፡ አነሣሥተው ፥ ጥቂት ፡ የልማት ፡ ሥራንና ፡ ያስተዳደር ፡ መሻሻልን ፡ አከናውነው ፥ አውራጃው ፡ የነበረበትን ፡ ያሥራ ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ የግብር ፡ ውዝፍ ፡ ዘጠኝ ፡ ወር ፡ ባልሞላ ፡ ወቅት ፡ ሊያስወግዱ ፡ ችለዋል ።

ግንቦት ፡ 27 ፡ ቀን ፡ 1944 ፡ ዓ.ም. ፥ *የዑጋዴን ፡ አውራጃ ፡ ገዥ* ፡ ተብለው ፡ ተሾሙ ። በዚሁ ፡ ኀላፊነታቸው ፥ ከጦርነቱ ፡ ወዲህ ፡ በብሪታንያ ፡ ወታደራዊ ፡ አስተዳደር ፡ ሥር ፡ የቈየውን ፡ *"ሀውድ"* ፡ የተባለውን ፡ ጠረፍ ፡ አካባቢ ፡ ተረክበዋል ።

እንዲሁም ፥ ዑጋዴን ፥ ጠረፍ ፡ አውራጃ ፡ እንደ ፡ መኾኑ ፡ መጠን ፥ በቀረጥ ፡ ኬላዎች ፡ አሰፋፈርና ፡ አሠራር ፥ ሕዝቡ ፡ አላግባብ ፡ መበደሉን ፡ ተገንዝበው ፥ የሥርዐት ፡ መስተካከልን ፡ አስፈጽመው ፡ ካውራጃ ፡ ገዢነታቸው ፡ ተነሡ ።

ኅዳር ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1948 ፡ ዓ.ም. ፥ ባገር ፡ ግዛት ፡ ሚኒስቴር ፥ *የርስትና ፡ የማዘጋጃ ፡ ቤቶች ፡ ምክትል ፡ ሚኒስትር* ፡ ተብለው ፡ ተሾሙ ።

ጥር ፡ 6 ፡ ቀን ፡ 1950 ፡ ዓ.ም. ፥ በመስኮብ ፥ የግርማዊነታቸው ፡ ልዩ ፡ መልክተኛና ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ኾነው ፡ ተሾሙ ። ነገር ፡ ግን ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ስላላሰናበቷቸው ፥ ካንድ ፡ ዓመት ፡ ጥበቃ ፡ በኋላ ፥ መጨረሻውን ፡ ሳይኼዱ ፡ ቀሩ ።

*ታኅሣሥ* ፡ 11 ፡ ቀን ፡ 1951 ፡ ዓ.ም. ፥ *የሜጀር ፡ ጀኔራልነት ፡ ማዕረግ* ፡ ተሰጣቸው ።

*መጋቢት* ፡ 9 ፡ ቀን ፡ 1951 ፡ ዓ.ም. ፥ *የብሔራዊ ፡ ጦር ፡ ኤታ ፡ ማዦር ፡ ሹም* ፡ ኾነው ፡ ተሾሙ ። ቀጥሎም ፥ ሚያዝያ ፡ 17 ፡ ቀን ፡ 1951 ፡ ዓ.ም. ፥ በመከላከያ ፡ ሚኒስቴር ፡ *ሚኒስትር ፡ ዴታ* ፡ ኾነው ፡ ተሾሙ ። ነገር ፡ ግን ፥ ሚኒስቴራቸው ፡ ሊኖረው ፡ ከሚገባው ፡ ድርጅታዊ ፡ ምላት ፡ ተራቍቶ ፥ ሥራ ፡ የማያሠራ ፡ ኾኖ ፡ ቢያገኙት ፥ አስፈላጊው ፡ መሟላት ፡ እንዲደረግ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጠየቁ ። ጥያቄያቸውም ፡ ተገቢውን ፡ ምላሽ ፡ ማጣቱን ፡ አይተው *፦ መንግሥትን ፡ ለመጠበቅ ፡ የቆመው ፡ ሰራዊት ፡ መንግሥትን ፡ ለመገልበጥ ፡ በደረሰበት ፡ ጊዜ ፥ መከልከል ፡ ቢያቅተኝ ፥ ዐብሬ ፡ አልገለብጥም ፤ ስለዚሀ ፡ ከዛሬ ፡ ዠምሮ ፡ ሥራዬን ፡ ትቻለኹ ፤* የሚል ፡ የሥራ ፡ መሰናበቻቸውን ፡

ቢያቀርቡም ፥ ንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ ሳይቀበሉት ፡ ቀሩ ። ገኔራሉም ፥ ፊት ፡ ዐቅደውት ፡ የነበረውን ፡ ጥናትና ፡ ድርጅታዊ ፡ ሥራ ፡ ለመወጠን ፡ ዕድሉን ፡ ስላገኙ ፥ ስለኢትዮጵያ ፡ አጠቃላይ ፡ ጊዜያዊ ፡ ኹኔታ ፡ ከየሚኒስቴሩና ፡ ከየጽሕፈት ፡ ቤቱ ፡ መረጃ ፡ እየጠየቁ ፥ ጥናታቸውን ፡ አጠናቀቁ ። የጥናቱም ፡ ዐይነተኛ ፡ ጭብጥ ፥ *ንጉሥ ፡ ነገሥታዊው ፡ ዘውድ ፡ እንደተጠበቀ ፡ ኾኖ ፥ ፈጻሚው ፡ ሥልጣን ፡ በሕዝብ ፡ በሚሾምና ፡ በሚሻር ፡ ጠቅላይ ፡ ሚኒስትር ፡ እጅ ፡ ይኹን ፡ የሚል* ፡ ነበር ። ይኸንኑ ፡ ግዛታዊና ፡ አስተዳደራዊ ፡ ጥናት ፥ ከለውጥ ፡ ሐሳብ ፡ ጋራ ፥ በማመዛዘኛ ፡ መልክ ፡ ለንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ ካቀረቡ ፡ በኋላ ፥ ተፈላጊው ፡ መሻሻል ፡ የማይፈጸም ፡ መኾኑን ፡ ስለ ፡ ተረዱ ፥ አያት ፡ ቅድም ፡ አያቶቻቸው ፡ የቆሙለትና ፡ የሞቱለት ፡ ዐልጋ ፡ አኹንም ፡ በጠቅላላው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነት ፡ ብቻ ፡ የሚጸናና ፡ የሚድን ፡ መኾኑን ፡ አምነው ፥ *"ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፥ የዠግኖች ፡ ማኅበር"* ፡ የተሠኘውን ፥ ባርበኝነት ፡ ዘመን ፡ ኢትዮጵያን ፡ የታደገ ፡ ሕዝባዊ ፡ ድርጅት ፥ ዓላማውንና ፡ አሠራሩን ፡ ሀገራዊ ፡ አድርጎ ፡ ዐድሶ ፡ ለማቋቋም ፡ ወሰኑ ።

በዚሁ ፡ ዘመን ፥ ከዚህም ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፥ አንዳንድ ፡ በቅርብ ፡ የሚያውቋቸውና ፡ የሚያምኗቸው ፡ መኰንኖች ፥ ያዬ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴን ፡ መንግሥት ፡ የመገልበጥና ፡ ዐዲስ ፡ መንግሥት ፡ የመመሥረት ፡ ሐሳባቸውን ፡ ያካፍሏቸው ፡ ነበርና ፥ ያመፃ ፡ ሐሳብን ፡ አጥብቀው ፡ በማውገዝ ፥ *"ሥራችን ፡ ኹሉ ፡ ለኢትዮጵያና ፡ ለንጉሥ ፡ ነገሥቱ ፡ በመታመን ፡ መኾን ፡ አለበት ፤ ተቃዉሟችንን ፡ ደግሞ ፡ በግልጽ ፡ እያስታወቅንና ፡ እያሰማን ፡ እንጂ ፥ በክዳት ፡ አንዳችም ፡ ነገር ፡ ለመሥራት ፡ አልስማማም"* ፡ በማለት ፡ ሐሳቡን ፡ ገፍተውታል ። ብዙ ፡ ሳይቈይ ፥ በታኅሣሥ ፡ ወር ፡ 1953 ፡ ዓ.ም. ፥ ያልጋ ፡ ግልበጣ ፡ ሙከራው ፡ በጥቂት ፡ መኰንኖችና ፡ ሲቪሎች ፡ ተዠምሮ ፡ ቀደማቸው ።

ሙከራውም ፥ ከብዙ ፡ ሰው ፡ ዕልቂት ፡ በኋላ ፡ ከሸፈ ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እንደ ፡ ራስ ፡ አበበ ፡ አረጋይ ፡ ያሉትን ፡ ያገር ፡ ዋልታዎች ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዐጣች ።

የፈሩት ፡ ጥፋት ፡ በመድረሱና ፡ የኢትዮጵያ ፡ አጠቃላይ ፡ የግዛት ፡ አዝማሚያ ፥ ከውጭም ፡ በሚወረወር ፡ ጥቃት ፥ ከውስጥም ፡ በሚነሣ ፡ ነውጥ ፥ ወደከፋ ፡ አግጣጫ ፡ በማምራቱ ፥ ሌ. ፡ ገኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከሥራ ፡ ባልደረቦቻቸውና ፡ ከዕውቅ ፡ አገር ፡ አፍቃሪዎች ፡ ጋራ ፥ *"ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፥ ሀገራዊ ፡ የዠግኖች ፡ ማኅበርን"* ፡ በታደሰ ፡ ሀገራዊ ፡ ዓላማና ፡ በተሻሻለ ፡ ደንብ ፥ በሚያዝያ ፡ ወር ፡ 1954 ፡ ዓ.ም. ፡ አቋቋሙ ። ኾኖም ፥ ድርጅቱ ፡ እስከ ፡ ሠኔ ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 1956 ፡ ዓ.ም. ፡ ድረስ ፡ ከመንግሥት ፡ ዕውቅናን ፡ ስላላገኘ ፥ ሥራው ፡ በዚሁ ፡ ምክንያት ፡ ለጊዜው ፡ ተገታ ።

ግንቦት ፡ 3 ፡ ቀን ፡ 1954 ፡ ዓ.ም. ፥ *የስሜንና ፡ በጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥ* ፡ ተብለው ፡ ተሹመው ፥ ሠኔ ፡ 7 ፡ ቀን ፡ 1954 ፡ ዓ.ም. ፥ *የሌ.ፍተና ፡ ገኔራልነት ፡ ማዕርግ* ፡ ተሰጣቸው ። ጎንደር ፡ እንደ ፡ ገቡም ፥

*"አሀያ ፡ መጣች ፡ ተጭና ፡ ሞፈር ፤*
*በነጋ ፡ ጊዜ ፥ እኽል ፡ እንዳፈር ። "*

በሚል ፡ ትንቢታዊ ፡ ቃል ፡ ሕዝቡ ፡ ተቀበላቸው ። ባመቱም ፤

*"አሀያ ፡ መጣች ፡ ተጭና ፡ ኮዳ ፤*
*በነጋ ፡ ጊዜ ፡ ሸንታል ፡ ፈነዳ ። "*

ሲል ፡ ዕረኛ ፡ ዘፈነ ። እንደ ፡ ንግርቱም ፥ በጠቅላይ ፡ ገዢነታቸው ፡ ዘመን ፥ አዝመራው ፡ እጅግ ፡ ተዋጥቶ ፥ የጥጋብ ፡ ዘመን ፡ ኾነ ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ የብሪታንያ ፡ ንግሥት ፡ ዳግማዊት ፡ ኤልሳቤጥን ፡ ጎንደርን ፡ አስጐብኝተው ፡ እንደ ፡ ጨረሱ ፥ የስሜንና ፡ በጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥ ፡ ሊ.. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ አዘዞ ፡ አየር–ወደብ ፡ ሲሸኟቸው ፥ 1957 ፡ ዓ.ም. ።




ሊ.. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ኮንጎ ፡ ዘምቶ ፡ የተመለሰውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰራዊት ፡ ሲጐበኙ ፤ ጎንደር ፡ 1955 ፡ ዓ.ም ።

በስሜንና ፡ በጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥነታቸው ፡ ከሠሯቸው ፡ ሥራዎች ፡ አንዱ ፡ በበጌምድርና ፡ በስሜን ፡ አውራጃዎች ፡ መኻከል ፡ ይደረግ ፡ የነበረው ፡ የግብር ፡ አመሳሶ ፡ ተወግዶ ፥ የኹለቱም ፡ አወራጃዎች ፡ ሕዝብ ፡ ባንድ ፡ የግብር ፡ ሥርዐት ፡ እንዲተካከል ፡ ማድረጋቸው ፡ ነው ። ይኸንኑም ፡ መተካከል ፥ *"ገባርና ፡ ድግር ፡ ሲተካከል ፡ ያምር"* ፡ ብሎ ፡

ሕዝቡ ፡ በደስታ ፡ ተቀበለው ።

ኾኖም ፥ ደግ ፡ ሥራ ፡ የሚሠራን ፡ ኹሉ ፥ ጸላኤ ፡ ሠናያት ፡ ተከታትሎ ፡ ሳይተናኰለው ፡ አይቀርምና ፥ በጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴም ፡ ላይ ፡ እንዲሁ ፡ ብዙ ፡ ክስና ፡ ፈተና ፡ ደረሰባቸው ። በባህሉ ፡ ብስለት ፡ ማንም ፡ የማይልቀው ፡ የጎንደር ፡ ሕዝብ ፥ ነገሩ ፡ በቅጽበት ፡ ገብቶት ፥ ዳር ፡ እስከ ፡ ዳር ፡ ጠቅላይ ፡ ገዢውን ፡ ዐቅፎ ፡ ለተፋጠነ ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ በተሰለፈበት ፡ ወቅት ፥ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በሽረት ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለሱ ።


ታላቅ ፡ ወንድማቸው ፡ ፊታውራሪ ፡ ማሞ ፡ አሸኔ ።


ሊ. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከወንድሞቻቸውና ፡ ወዳጆቻቸው ፡ ጋራ ፤ ዐዲስ ፡ አበባ ፥ 1954 ፡ ዓ.ም. ።
(*ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፥* ልጅ ፡ ለማ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ደጃዝማች ፡ ግርማቸው ፡ ተክለ ፡ ሐዋርያት ፥ ሊ. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ልጅ ፡ ታደሰ ፡ ግዛው ፥ ሊ. ፡ ጀኔራል ፡ መርድ ፡ መንገሻ ፥ ቀኛዝማች ፡ መኰንን ፡ ነጋሽ ። )

ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ እንደ ፡ ተመለሱም ፥ ቀደም ፡ ሲል ፡ ተቋቁሞ ፥ ሠኔ ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 1956 ፡

*ዓ.ም. ፡ ሕጋዊ ፡ ዕውቅና ፡ ያገኘው ፥ የጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ የዠግኖች ፡ ማኅበር ፡ ጠቅላይ ፡ ሥራ ፡ አመራር ፡ ደርግ ፡ ሊቀመንበር* ፡ ኾነው ፥ የማኅበሩን ፡ ሥራ ፡ በሰፊው ፡ በማንቀሳቀስ ፥ ባጪር ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ 4000 ፡ የፈረሙ ፡ አባላትን ፡ ከጠቅላላው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኅብረተሰብ ፡ እንዳስገኙ ፥ ከሕግ ፡ ውጭ ፥ የድርጅቱ ፡ ጽሕፈት ፡ ቤት ፡ በጸጥታ ፡ ኀይሎች ፡ እንዲዘጋ ፡ ተደረገ ። ለፍጹም ፡ ሰላማዊና ፡ ሀገራዊ ፡ ዓላማ ፡ በግልጽና ፡ በሕጋዊነት ፡ የተዠመረውም ፡ ይህ ፡ ደኅኛ ፡ ሥራ ፥ ሊያገለግለው ፡ በተነሣለት ፡ መንግሥታዊ ፡ ኀይል ፡ አላግባብ ፡ ተሰናከለ ። የማኅበሩም ፡ ጠቅላይ ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ ደርግ ፥ መብቱን ፡ ለማስከበር ፥ እስካብዮቱ ፡ ዋዜማ ፡ ድረስ ፡ ጉዳዩን ፡ ለፍርድ ፡ ቤት ፡ አቅርቦ ፡ ሲሟገት ፡ ቈየ ።

*መጋቢት* ፡ 9 ፡ ቀን ፡ 1957 ፡ ዓ.ም. ፥ *የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል* ፡ ኾነው ፡ ተሾሙ ። በምክር ፡ ቤቱ ፥ ከፍተኛ ፡ ተሰሚነትን ፡ ከማትረፍም ፡ በላይ ፥ በርከት ፡ ያሉ ፡ የሕግ ፡ ማሻሻያዎችን ፡ (በተለይ ፡ ስለ ፡ ርስት ፥ ስለ ፡ ጢሰኛና ፡ ባለርስት ፥ ስለ ፡ መድን ፡ ሥርዐት) ፥ ውሳኔዎችን ፡ (በተለይ ፡ ስለአኾስም ፡ ሐውልትና ፡ በግፍ ፡ ስለተወሰዱ ፡ ቅርሳቅርሶች ፡ ከኢጣሊያ ፡ መመለስ) ፡ በሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አስጸድቀዋል ። እንዲሁም ፥ ባሜሪካ ፡ መንግሥት ፡ ጋባዥነት ፥ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባላት ፡ ቡድን ፡ ጋራ ፡ ባሜሪካ ፡ ያንድ ፡ ወር ፡ የጥናት ፡ ጕብኝት ፡ አከናውነዋል ።

ግንቦት ፡ 10 ፡ ቀን ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ፥ የይፋት ፡ ልማት ፡ ማኅበርን ፡ ከብዙ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ጋራ ፡ አቋቁመው ፥ በሊቀ ፡ መንበርነት ፡ መርተዋል ። የይፋት ፡ ልማት ፡ ማኅበር ፥ ክርስቲያኑንም ፡ እስላሙንም ፥ ባንድ ፡ ሀገራዊ ፡ የልማት ፡ መንፈስ ፡ ያወሐደ ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፥ ባምስት ፡ ዓመቱ ፡ የፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ የወረራ ፡ ዘመን ፡ የይፋት ፡ አውራጃ ፡ የባሰ ፡ ከተደበደቡትና ፡ ከጠፉት ፡ አውራጆች ፡ አንዱ ፡ በመኾኑ ፥ አውራጃውን ፡ መልሶ ፡ ለማቋቋም ፡ ፈቃደኛ ፡ ኾነው ፡ ተሰልፈውለታል ።

ባለመታደል ፥ ማኅበሩ ፥ ሕጋዊና ፡ ግልጽ ፡ በኾነ ፡ መንገድ ፥ ያመራር ፡ ሕዋሳቱን ፡ አብጅቶ ፥ ለልማት ፡ በሚንቀሳቀስበት ፡ ወቅት ፥ የማኅበሩ ፡ የዐፈሮቹ ፡ ተወካይ ፡ ቀኛዝማች ፡ ሳዖሌ ፡ ሆቴ ፥ ሸዋ ፡ ሮቢት ፡ ላይ ፥ የማኅበሩ ፡ ዋና ፡ ጸሓፊ ፥ አቶ ፡ ከበደ ፡ ብዙዬ ፡ ደግሞ ፡ ደብረ ፡ ሲና ፡ ላይ ፡ ባደጋ ፡ ሞቱ ። ከመንግሥት ፡ ሥራ ፡ ተገልለው ፡ ይፋት ፡ ይኖሩ ፡ የነበረው ፡ ሰመ ፡ ጥሩው ፡ ዐርበኛና ፥ የማኅበሩ ፡ ምክትል ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፥ ደጃዝማች ፡ ተሰማ ፡ ርገጤ ፥ በሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባልነት ፡ (ሴናተርነት) ፡ ሹመት ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ ተጠርተው ፡ ኼዱ ፥ ሊቀ ፡ መንበሩ ፥ ሊ. ፡ ገኔኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴም ፥ በአምባሳደርነት ፡ ወደ ፡ መግሪብ ፡ (ሞሮኮ) ፡ ተላኩ ፤ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ የማኅበሩ ፡ ሥራ ፥ በተነሣበት ፡ ግሥጋሤው ፡ ሳይቀጥል ፡ ቀረ ።

*መጋቢት* ፡ 25 ፡ ቀን ፡ 1962 ፡ ዓ.ም. ፥ *የሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ እንደራሴ* ፡ ኾነው ፡ ተሾሙ ። በወቅቱ ፡ ነዋሪነታቸው ፡ እሲዳሞ ፡ የነበረው ፡ ደራሲ ፡ አክሎግ ፡ ዘለቀ ፥ የገኔኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ሲዳሞ ፡ መምጣት ፡ እሕዝቡ ፡ ዘንድ ፡ የዘራውን ፡ ተስፋ ፡ ለመግለጽ ፤

*በባሌ ፡ ዑጋዴ ፥ በጎንደር ፡ አስመራ ፡*
*እየነጋ ፡ ሲኼድ ፥ ሥራው ፡ እያበራ ፥*
*በየደረሰበት ፡ ሀገሩን ፡ ሲያኰራ ፥*
*ዕድል ፡ ሲያጋጥመው ፡ እንዲሁ ፡ በተራ ፥*
*ብቅ ፡ አለ ፡ በደቡብ ፡ ለሲዳሞ ፡ ጮራ ።*

ሲሉ ፡ ተቀኝተውላቸዋል ።

ሲዳሞ ፡ በቈየበት ፡ አንድ ፡ ዓመት ፡ ከሦስት ፡ ወር ፥ በመሬት ፡ ይዞታና ፡ ባስተዳደር ፡ ረገድ ፡ ይታዩ ፡ ለነበሩ ፡ ጕድለቶች ፥ ባጪር ፡ ጊዜ ፡ በተፈጸሙ ፡ ቀልጣፋ ፡ ርምጃዎች ፥ የሕዝቡን ፡ ውዴታ ፡ ያረኩ ፡ መሻሻሎችን ፡ አስገኝተዋል ።

እንዲሁም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በኬንያ ፡ መኻከል ፡ ያለውን ፡ ወሰን ፡ ለማካለል ፡ የተላከውን ፡ የውጭ ፡ ጕዳይ ፡ ሚኒስቴር ፡ ቡድን ፡— *የጠረፉ ፡ ስምምነት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ ታይቶ ፡ እስካልጸደቀ ፡ ድረስ ፥ አንዳች ፡ የማካለል ፡ ሥራ ፡ ሊካኼድ ፡ አይችልም* ፥ በማለት ፥ ቡድኑን ፡ ወዳዲስ ፡ አበባ ፡ መልሰውታል ።

ሲዳሞ ፡ በቈየበት ፡ ወቅት ፥ ኹለት ፡ ጊዜ ፡ ያኽል ፥ በእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፥ ከግድያ ፡ ሙከራ ፡ ተርፈዋል ።

ሐምሌ ፡ 13 ፡ ቀን ፡ 1963 ፡ ዓ.ም. ፥ *በመግሪብ ፡ የግርማዊነታቸው ፡* ልዩ ፡ *መልክተኛ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡* ኾነው ፡ ተሹመው ፥ እስከ ፡ ኅዳር ፡ 25 ፡ ቀን ፡ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ በዚሁ ፡ አገልግሎት ፡ ቈዩ ።

እውስጥ ፡ ኾኖ ፥ ላገሪቱ ፡ የሚበጀውን ፡ በነጻነት ፡ የመሥራቱን ፡ ዕድል ፡ ቢያጡ ፥ የውጭ ፡ አገሩ ፡ ጕዞ ፡ ምናልባት ፡ በዝግጅት ፡ ረገድ ፡ ይጠቅመኝ ፡ ይኾናል ፡ ብለው ፡ ምንም ፡ ሳያማርሩ ፥ ከነቤተሰባቸው ፡ መውጣቱን ፡ አልጠሉትም ። የኢትዮጵያን ፡ ግዛታዊ ፡ አዝማሚያ ፡ ጠልቀው ፡ ያወቁና ፡ የተረዱ ፡ ዐዛውንትም ፥ ከፊሎቹ ፡— *ለምን ፡ በንዲህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ርስዎን ፡ ያኽል ፡ ሰው ፡ ካገር ፡ ይባረራል ፡:* ብለው ፡ ሲያዝኑ ፥ ከፊሎቹ ፡ ደግሞ ፡— *ከፋኝም ፥ ደስ ፡ አለኝም ፡ ሳይሉ ፥ ወደተላኩበት ፡ አገር ፡ ይኺዱ ፤ እግዚአብሔር ፡ ላገር ፡ ሊያተርፍዎ ፡ ይኾናል ፤* እያሉ ፥ ተሰናበቷቸው ።

የፊተኞቹም ፡ የኋለኞቹም ፡ ማስተዋል ፥ እየቅል ፡ ይኹን ፡ እንጂ ፥ የኹሉም ፡ ሥጋት ፥ ብዙ ፡ ሳይቈይ ፥ ተረጋገጠ ፤ ያዬ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ መንግሥት ፥ ሥርዐተ ፡ ውርስ ፡ ሳይፈጸምለት ፥ ባ 1966–67 ፡ ዓ.ም. ፡ ተጠቃለለ ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ዐፄ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ላ 10 ኛው ፡ ያፍሪቃ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ ጉባኤ ፡ ርባጥ ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፥ የመግሪብ ፡ ንጉሥ ፡ ዳግማዊ ፡ ሐሰን ፡ ሲቀበሏቸው ።

መግሪብ ፡ በቈዩባቸው ፡ ሦስት ፡ ዓመታት ፥ ርባጥ ፡ ከተማ ፡ ከተካኼደው ፡ 10 ኛ ፡ ያፍሪቃ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ ጉባኤ ፥ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ ተሳትፈዋል ።

እንዲሁም ፥ ከመግሪብ ፡ ንጉሥ ፡ ከዳግማዊ ፡ ሐሰን ፥ ከአልጀዛይሩ ፡ ርእሰ ፡ መንግሥት ፡ ሁዋሪ ፡ ቡምዲየን ፥ ከቱኒስያው ፡ ርእሰ ፡ መንግሥት ፡ ሐቢብ ፡ ቡርጊባና ፡ ከሞሪታንያው ፡ ርእሰ ፡ መንግሥት ፡ አህመድ ፡ ኡልድ ፡ ዳዳ ፡ ጋራ ፥ ያፍሪቃ ፡ መንግሥታት ፡ ከእስራኤል ፡ ጋራ ፡ ያላቸውን ፡ መባሕታዊ ፡ ግንኙነት ፡ ስለማቋረጥ ፡ ጕዳይ ፡ ተነጋግረው ፥ ብርቱ ፡ ማመዛዘኛ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ አስተላልፈዋል ።



ሌ.. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ከባልተቤታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፥ በመግሪብ ፡ የደቡብ ፡ ኮሪያ ፡ እንደራሴና ፡ ባልተቤታቸው ፡ አደረጉላቸው ፡ ግብዣ ፡ ላይ ፤ ርባጥ ፥ 1965 ፡ ዓ.ም. ።

ቀደም ፡ ሲል ፡ በአእምሯቸው ፡ ይጕላላ ፡ የነበረውና ፥ ላዲሱ ፡ ትውልድ ፡ ለማሳወቅ ፡ ይጨነቁለት ፡ የነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ትውፊታዊ ፡ የግዛት ፡ ፍልስፍና ፥ መግሪብ ፡ በቈዩበት ፡ ዘመን ፥ ከመቼውም ፡ ይበልጥ ፡ ጐልቶና ፡ ጠርቶ ፡ ስለ ፡ ታያቸው ፥ ሞልቶና ፡

በቅቶ ፡ ስለ ፡ ተገነዘባቸውም ፥ ወዲያዉኑ ፡ በጽሑፍ ፡ ለማኖር ፡ ተነሡ ። በብርዕ ፡ ያረቀቁትን ፡ ጽሑፍ ፥ ባልተቤታቸው ፡ ክብርት ፡ ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጽሕፈት ፡ መኪና ፡ እየመቱላቸው ፥ አሰናድተው ፥ "ርትዓዊ ፡ ኹነት" ፡ የተሠኘ ፡ መጽሐፋቸውን ፡ ደረሱ ።

ባ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ በኢትዮጵያ ፡ የደረሰው ፡ ግዛታዊ ፡ ነውጥ ፥ ባዠማመሩ ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ተጨብጦ ፡ የኖረውን ፡ ግዛታዊ ፡ ሥልጣን ፥ ሕዝብ ፡ በእግዚእናው ፡ መልሶ ፡ እጁ ፡ ለማስገባት ፡ ያደረገው ፡ ደገኛ ፡ እንቅስቃሴ ፡ መኾኑ ፡ ቢታመንም ፥ በተለይ ፡ ያዲስ ፡ አበባን ፡ ደኅንነት ፡ ለመጠበቅ ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ የተቋቋመው ፡ ወታደራዊ ፡ ደርግ ፥ የተሰጠውን ፡ የተወሰነ ፡ ኀላፊነት ፡ ተራምዶ ፥ የመንግሥትነትን ፡ ሥልጣን ፡ በእጁ ፡ መናኛ ፡ ከያዘ ፡ በኋላ ፡ የፈጸማቸውን ፡ ያንባ ፡ ገነን ፡ ድርጊቶች ፥ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ አጥብቀው ፡ አወገዙ ። ከወታደራዊው ፡ ደርግ ፡ ቀንበር ፡ ውጭ ፡ ኾኖ ፡ ለመታገልም ፥ ቤተሰባቸውን ፡ ይዘው ፡ ወደ ፡ ብሪታንያ ፥ ታኅሣሥ ፡ 28 ፡ ቀን ፡ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ ተሰደዱ ።

ከመሰደዳቸውም ፡ በፊት ፥ ከተሰደዱም ፡ በኋላ ፥ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዐይነተኞች ፡ አፈ ፡ ጉባኤዎች ፡ በተከታታይ ፡ የተላከባቸውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ የመታደግ ፡ ዐደራ ፡ መልክት ፡ እዳር ፡ ለማድረስ ፥ በስደት ፡ ካገኟቸው ፡ ፈቃደኞች ፡ ወገኖቻቸው ፡ ጋራ ፡ መክረውና ፡ ዘክረው ፡ በተስማሙበት ፡ መሠረት ፥ "የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት" ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.)ን ፥ ሐምሌ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1967 ፡ ዓ.ም. ፡ ሎንዶን ፡ ላይ ፡ አቋቋሙ ።

ኢትዮጵያ፡ታበጽሕ፡እደዊሃ፡ኀበ፡እግዚአብሔር።

**ኢ ሀ ሥ አ**

(የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ ትእምርተ ፡ ቃል ። )

እንሆ ፥ ክቡር ፡ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ከልጅነት ፡ ዘመናቸው ፡ አንሥቶ ፡ እስካረጋዊነት ፡ ዘመናቸው ፡ ድረስ ፥ እግዚአብሔር ፡ በሰጣቸው ፡ ጊዜና ፡ ዐቅም ፥ አገራቸውን ፡ በሚጠቅምና ፡ በሚመለከት ፡ ጉዳይ ፡ በተሰማሩበት ፡ ሥራ ፡ ኹሉ ፥ አስተዋይነትንና ፡ ችሎታን ፥ ታማኝና ፡ ቅን ፡ መንፈስን ፥ ፍትሓዊና ፡ ግልጽ ፡ አሠራርን ፥ እውነተኛና ፡ ቸር ፡ ልቦናን ፡ አሳይተዋል ። በኼዱበት ፡ ኹሉ ፡ ተወዳጅነትን ፡ አትርፈዋል ። በቅርብ ፡ ያወቃቸው ፡ ቀርቶ ፥ በሩቅ ፡ ዝናቸውን ፡ የሰማም ፥ በአርኣያቸው ፡

ይደነቃል ።

ክቡር ፡ ሊ.. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ዘወትር ፡ የማይለያቸው ፡ ፈገግታቸው ፡ አስቀድሞ ፡ እንደሚናገረው ፥ በሥራም ፡ ኾነ ፡ በወንድምነት ፥ በእኅትነት ፥ በወዳጅነት ፡ ዐብሯቸው ፡ ለኖረ ፡ ቀርቶ ፥ ዐዲስ ፡ ለተዋወቃቸውም ፡ እንኳ ፥ ወዲያው ፡ ግዙፍ ፡ ኾኖ ፡ የሚታይ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ በቃላት ፡ ሊነገር ፡ ሊሰፈር ፡ የማይችለውን ፡ የፍቅር ፡ የታማኝነት ፥ የቸርነት ፡ የትሕትና ፥ የብልኀነት ፡ የብስለት ፥ የጨዋነት ፡ የልጨኝነት ፥ የርኅሩኅነት ፡ የፍትሐዊነት ፥ የዠግንነት ፡ ታላቅ ፡ ሰብእናን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የታደሉ ፡ ሰው ፡ ናቸው ። ታሪካቸውም ፡ ይኸንኑ ፡ የሚገልጽ ፡ ሕያው ፡ ምስክር ፡ ነው ።

በሕይወታቸው ፡ ዐያሌ ፡ መከራና ፡ ፈተና ፡ ቢደርሱባቸውም ፥ አንድም ፡ ቀን ፡ ሲማረሩ ፡ አልተሰሙም ። ተስፋ ፡ መቍረጥ ፡ የሚሉት ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ አያውቃቸውም ፤ አያውቁትም ። ዘወትር ፡ በሚታደጋቸው ፡ አምላክ ፡ ያላቸውን ፡ እምነት ፡ አንድም ፡ ቀን ፡ አላጓደሉ ፤ ርሱም ፡ አላሳፈራቸው ፥ አያሳፍራቸውም ።

ጨዋታቸው ፡ የማይሰለች ፡ የማይጠገብ ፥ ተናፋቂ ፤ የሚናገሩትም ፡ ኾነ ፡ የሚጽፉት ፥ በቃልም ፡ በመንፈስም ፡ የታረመ ፥ በሕይወት ፡ ተመክሮ ፡ የበሰለ ፥ በዕውቀት ፡ የዳበረ ፥ በማስተዋል ፡ የረቀቀ ፥ ለዛው ፡ ያማረ ፡ ነው ።

የሚያደንቋቸውን ፡ የሌሎችን ፡ ታሪክና ፡ ገድል ፡ ለመጻፍ ፡ ይጓጉ ፥ ወይም ፡ ባለመጻፋቸው ፡ ይንገበገቡ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፥ የራሳቸውን ፡ ታሪክ ፡ መጻፍ ፡ አንድም ፡ ደቂቃ ፡ አልከጀላቸው ።

*"ሣህሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በጊዜሁ"* ፡ ነውና ፥ ያ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ድኅነት ፡ ቀን ፡ እስኪመጣ ፥ ለተሰለፉለት ፡ የተቀደሰ ፡ ሀገራዊ ፡ ዓላማ ፥ በተሳተፉበት ፡ ተግባር ፡ ኹሉ ፥ ለትውልዶች ፡ ትምህርትና ፡ ዐይነተኛ ፡ መሣሪያ ፡ የሚኾኑ ፡ አስደናቂ ፡ ሥራዎችንም ፡ ሐሳቦችንም ፥ በክንዋኔም ፥ በጽሑፍም ፥ በቃልም ፡ አኑረዋል ።

ሕይወታቸው ፡ በአርኣያነቱ ፡ ሲጠቀስና ፡ ሲወሳ ፡ ይኖራል ።

## 4
## ክንዋኔዎችና ፡ ዕቅዶች

እስካኹን ፡ እጅግ ፡ ጥቂቶቹ ፡ ብቻ ፡ ለመታተም ፡ ይብቁ ፡ እንጂ ፥ ስለ ፡ ታሪክም ፡ ኾነ ፡ ስለግዛት ፡ ፍልስፍና ፥ ስለ ፡ ቀለምም ፡ ኾነ ፡ ስለ ፡ ቋንቋ ፥ ዐያሌ ፡ ጽሑፎችን ፡ ደርሰዋል ።

ካሳተሟቸው ፡ መጻሕፍት ፡ መኻከል ፡ የመዠመሪያው ፥ *"ከታሪክ ፡ አንድ ፡ ገጽ"* ፡ የተሠኘ ፥ ላርበኝነት ፡ ዘመን ፡ መታሰቢያ ፡ አስመራ ፡ ኾነው ፡ ደርሰውት ፥ ባ 1956 ፡ ዓ.ም. ፡ ያሳተሙት ፡ ዐጪር ፡ የግጥም ፡ መጽሐፍ ፡ ይገኛል ። እንዲሁም ፥ ባ 1986 ዓ.ም. ፡ *"ርትዓዊ ፡ ኹነት"* ፡ የተሠኘውን ፡ የግዛት ፡ ፍልስፍና ፡ መጽሐፍ ፡ አሳትመዋል ።

ተጽፈው ፡ የተዘጋጁ ፥ ነገር ፡ ግን ፡ ገና ፡ ያልታተሙ ፡ ሌሎች ፡ መጽሐፎች ፡ አሏቸው ፤ ከነዚህ ፡ ውስጥ ፤

- *አቢስያ ፥ ጥንተ ፡ ኢትዮጵያ ፤*
- *ሥልጣንና ፡ ሥልጣኔ ፤*
- *ታሪካዊ ፡ ዐጪር ፡ ማስታወሻ ፤*
- *የይፋት ፡ ትዝታ ፤*

- *ያገር፡ ፍቅር፡ መዝሙሮች*፤

ይገኙባቸዋል።

የተወሰኑ፡ ሀገራውያንና፡ ማኅበራውያን፡ ድርጅቶችን፡ አቋቁመዋል፤ ብዙዎቹንም፡ በሊቀ፡ መንበርነት፡ መርተዋል። ከነዚህ፡ ውስጥ፤

- *ጥንታዊት፡ ኢትዮጵያ፡ ሀገራዊ፡ የዠግኖች፡ ማኅበር፡* (ሚያዝያ፡ 1956፡ ዓ.ም.)፥ ሊቀ፡ መንበር፤
- *የይፋት፡ ልማት፡ ሕዝባዊ፡ ኅብረት፡* (ግንቦት፡ 10፡ 1960፡ ዓ.ም.)፤ ሊቀ፡ መንበር፤
- *የኢትዮጵያውያን፡ ሀገራዊ፡ ሥልጡንሕዝባዊ፡ አንድነት፥* ሐምሌ፡ 1፡ ቀን፡ 1967፡ ዓ.ም.፥ ሊቀ፡ መንበር፤ (ሚያዝያ፡ 10፡ 1982፡ ዓ.ም.)፡ የጊዜያዊ፡ ከዋኝ፡ ምክር፡ ሊቀ፡ መንበር፤
- *የኢትዮጵያ፡ ዐውደ፡ ቀለም፡* (መስከረም፡ 24፡ ቀን፡ 1990፡ ዓ.ም.)፥ ሊቀ፡ መንበር።

ባ 1954፡ ዓ.ም.፥ *የኢትዮጵያ፡ እግር፡ ኳስ፡ ፌደሬሽን፡* ሊቀ፡ መንበር፡ በነበሩበት፡ ወቅት፥ ኢትዮጵያ፡ ያፍሪቃ፡ ዋንጫን፡ ለመዠመሪያ፡ ጊዜ፡ አሸንፋለች።

በብፁዕ፡ ወቅዱስ፡ አቡነ፡ ባስልዮስ፡ ርእሰ፡ ሊቃነ፡ ጳጳሳት፡ ወፓትረያርክ፡ ዘኢትዮጵያ፡ ሠያሚነት፥ የኢትዮጵያ፡ ኦርቶዶክስ፡ ተዋሕዶ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ሥጋዊ፡ አስተዳደር፡ ጉባኤ፡ አባል፡ ኾነው፡ ለጥቂት፡ ዓመት፡ አገልግለዋል።

## 5
## ሽልማቶች

ከኢትዮጵያ፡ ንጉሠ፡ ነገሥት፡ መንግሥት፤

- ያርበኝነት፡ ሜዳይ፥ ጥር፡ 12፡ ቀን፡ 1937፡ ዓ.ም.፤
- የቅዱስ፡ ጊዮርጊስ፡ የጦር፡ ሜዳ፡ ሜዳይ፥ ጥር፡ 12፡ ቀን፡ 1937፡ ዓ.ም.፤
- የዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ የመኰንን፡ ደረጃ፡ ሊሻን፥ መጋቢት፡ 12፡ ቀን፡ 1943፡ ዓ.ም.፤
- የኢትዮጵያ፡ የክብር፡ ኮከብ፡ ታላቅ፡ መኰንን፥ ሚያዝያ፡ 27፡ ቀን፡ 1943፡ ዓ.ም.፤
- የድል፡ ኮከብ፡ ሜዳይ፥ ሚያዝያ፡ 16፡ ቀን፡ 1948፡ ዓ.ም.፤
- የዳግማዊ፡ ምኒልክ፡ ኮርዶን፡ ኒሻን፥ ሚያዝያ፡ 27፡ ቀን፡ 1958፡ ዓ.ም.።

የውጭ፡ መንግሥታት፡ ከሸለሟቸው፡ ውስጥ፤

- ከስዊድን፡ መንግሥት፥ Kömmendor med stora av Kungl. Svärdsorden፥ የካቲት፡ 1952፡ ዓ.ም.፤
- ከታላቋ፡ ብሪታንያ፡ መንግሥት፥ Knight Commander of the Victoria Order፥ 1957፡ ዓ.ም.፤

ይገኙባቸዋል።

## 6

## ቤተሰብ



ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴና ፡ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ የጋብቻቸውን ፡ ኢዮቤላዊ ፡ መታሰቢያ ፥ እሎንዶን ፡ ደብረ ፡ ጽዮን ፡ ቅድስት ፡ ማርያም ፡ የኢትዮጵያ ፡ ኦርቶዶክስ ፡ ተዋሕዶ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሲያከብሩ ፤ የጰራቅሊጦስ ፡ (በዓለ ፡ ኀምሳ) ፡ ዕለት ፥ ሠኔ ፡ 3 ፡ ቀን ፡ 1993 ፡ ዓ.ም. ።

**ከባልተቤታቸው ፡ ከክብርት ፡ ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሰባት ፡ ልጆች ፡ ወልደዋል ፥ ሦስት ፡ የልጅ ፡ ልጆችንም ፡ አይተዋል ።**



ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴና ፡ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥
አትክልታቸው ፡ ውስጥ ፤ ክሮይድን ፡ (ብሪታንያ) ።

*"የማይቀረው ፡ ዕጣ ፥ መለየት ፡ ክፉ ፡ ነው ፤*
*አዬ ፡ አባብዬ ፥ አጐደልከን ፡ ምነው ፦ " (ማ.ነ.)*



*(ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፥ ፊት)* ፤ ዶክተር ፡ ድልወንበራ ፡ ነጋ ፥ ወይዘሮ ፡ ሙኒት ፡ መርድ ፥ ወይዘሮ ፡ ብርሃኔ ፡ ነጋ ፥ ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ። *(ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፥ ኋላ)* ፤ ልጅ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፥ ልጅ ፡ አውሳቤ ፡ ነጋ ፥ ዶክተር ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ነጋ ፥ ልጅ ፡ ዳጨው ፡ መርድ ፥ መሐንዲስ ፡ ጎሕ ፡ ነጋ ።

ልጆቻቸው ፤
- ዶክተር ፡ ድልወንበራ ፡ ነጋ ፤
- ወይዘሮ ፡ ብርሃኔ ፡ ነጋ ፤
- ዶክተር ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ነጋ ፤
- ወይዘሮ ፡ ማናለብሽ ፡ ነጋ ፤
- መሐንዲስ ፡ ጎሕ ፡ ነጋ ፤
- ልጅ ፡ ወሌ ፡ ነጋ ፤
- ልጅ ፡ አውሳቤ ፡ ነጋ ።

ከዶክተር ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ነጋና ፡ ከወይዘሮ ፡ ኤስቴር ፡ አርትሊብ ፡ የተወለዱት ፡ የልጅ ፡ ልጆቻቸው ፥ ወይዘሪት ፡ አበባ ፥ ወይዘሪት ፡ ሚላኤል ፥ ወይዘሪት ፡ የተሻ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ናቸው ።

## 7
## ዜና ፡ ዕረፍት



ሌ. ፡ ገቬኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ
(አባ ፡ ይባስ)
፲፱፻፲–፳፻ ፡ ዓ.ም. ፨

ዐብረን ፡ አሳልፈን ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ስደት ፥
አገራችን ፡ ገባን ፡ ብለን ፡ ስንደሰት ፥
ምነው ፡ አመለጡኝ ፡ ጥቂት ፡ ሳንሰነብት ∴

አገሬ ፡ ናፈቀኝ ፡ ሲሉ ፡ የነበረው ፡
ምን ፡ ጊዜ ፡ ፀሓይዋን ፡ ነፋሷን ፡ ጠግበው ፡ ነው ∴
መኼድ ፡ የቸኰሉት ፡ ከቶ ፡ ለምንድን ፡ ነው ∴

ያገርዎ ፡ ናፍቆት ፡ ምንጊዜ ፡ አለቀና ፡
ጣል ፡ አርገዋት ፡ ኼዱ ፥ ምነው ፡ እንደ ፡ ገና ∴

አልተሰነባበትን ፥ አላሉኝ ፡ ደኅና ፡ ዋይ ፤
እንዲያው ፡ ዝም ፡ ብለው ፡ መቅረትዎ ፡ ነው ፡ ወይ ∴

ከፈይ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ።

---

ክቡር ፡ ሌ.ገቬኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ 32 ፡ ዓመት ፡ በስደት ፡ ከቈዩ ፡ በኋላ ፥ ሚያዝያ ፡ 8 ፡ ቀን ፡ 1999 ፡ ዓ.ም. ፡ ከክብርት ፡ ባልተቤታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይል ፡ ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ውድ ፡ አገራቸው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመልሰው ፥ መዠመሪያ ፡ ቃሊቲ ፥ ከዚያም ፡ ዐዲስ ፡ አበባ ፡ ዓመት ፡ ተሥስት ፡ ወር ፡ ተቀምጠው ፥ በቤተሰብ ፥ በቤተ ፡ ዘመድና ፡ በወዳጅ ፡ ፍቅር ፡ ተከበው ፡ ከርመው ፥ ሐምሌ ፡ 15 ፡ ላ 16 ፡ አጥቢያ ፡ 2000 ፡ ዓ.ም. ፡ በድንገተኛ ፡ ሕመም ፡ ምክንያት ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ገብተው ፥ ሌሊቱን ፡ በሰላም ፡ ዐርፈዋል ።

ዳግመኛ ፡ በትንሣኤ ፡ እስከምንተያይ ፥ ቸር ፡ አምላክ ፡ ነፍሳቸውን ፡ እንዲምርልን ፥ በገነት ፡ ከአብርሃም ፡ ከይሥሐቅና ፡ ከያዕቆብ ፡ ጐን ፡ እንዲያሳርፍልን ፥ መንግሥተ ፡ ሰማያትንም ፡ እንዲያወርስልን ፡ እየለመን ፥ እንሰናበታቸዋለን ፨

ምን ፡ ዠግና ፡ ቢኾኑ ፥ ምን ፡ ደግ ፡ ቢኾኑ ፥ ሞት ፡ አይቀርም ፡ ለኛ ፤
አባ ፡ ይባስ ፡ ነጋ ፡ ዘንድሮስ ፡ ደከመው ፥ ጥቅልል ፡ ብሎ ፡ ተኛ ።
ኧረ ፡ አንገበገበኝ ፡ ዘንድሮስ ፡ መረረኝ ፥ ፈጀኝ ፡ እንጂ ፡ እሳት ፥
የትልቅ ፡ ወንድሜ ፡ ያባ ፡ ይባስ ፡ ሞት ።
ብወድቅ ፡ ብነሣ ፥ ብድኽ ፡ በጕልበቴ ፥ ባለቅሰው ፡ ባነባው ፥ ብጮኽ ፡ ከሰው ፡ መኻል ፥
ምኞቴ ፡ አልተሳካም ፤ መና ፡ ኾኖ ፡ ቀርቷል ።
እናቴም ፡ አባቴም ፥ ዕውቀቴም ፡ ትዳሬም ፥ እሱ ፡ ነበርና ፥
ብድሩንም ፡ ሳልከፍል ፥ አይቹም ፡ ሳልጠግበው ፥ ሞተብኝ ፡ ያ ፡ ዠግና ።
ዠግናው ፡ ማሞ ፡ አሽኔ ፥ አባ ፡ ተግብ ፡ ለማ ፥ አባ ፡ ይባስ ፡ ነጋ ፥
ደጉ ፡ ሰው ፡ ታደሰ ፡ ተከታትለው ፡ ኼደው ፡ አራት ፡ ወንድሞቼ ፥
የኔ ፡ ቀን ፡ እስኪደርስ ፡ ሳለቅስ ፡ እኖራለኹ ፥ ብቻዬን ፡ ቀርቼ ።

እኅትኽ ፡ የተሻ ፡ ወርቅ ፡ ግዛው ።

---

ነጋ ፥ ዠግና ፡ ነበልባል ።

አገር ፡ በነጻነት ፡ ጠብቀው ፡ ያቈዩ ፥
በዱር ፡ በበረሓው ፡ ፋሺስትን ፡ ያጋዩ ፥
በመልክ ፡ በመልኩ ፡ በዘመን ፡ ሲለዩ ፥
የኛ ፡ ኵራት ፡ ናቸው ፡ በታሪክ ፡ ሲታዩ ።
የዠግኖቹ ፡ ዠግና ፥ መብረቅ ፡ ወይ ፡ ነበልባል ፥
በመላ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዝናው ፡ ተሠራጭቷል ።
አገር ፡ ወገን ፡ ሲያምጥ ፡ በሠርክ ፡ በሌሊት ፥
ጨለማው ፡ ገፈፈ ፥ ነጋ ፡ ደርሶለት ።
ነገም ፡ ለዛሬ ፡ አለው ፥ ዛሬም ፡ ለትላንት ፤
ማን ፡ አለኝ ፡ መጽናኛ ፥ እስኪ ፡ በኔ ፡ ሞት ፡
ነጋ ፡ መመኪያዬ ፥ የኔ ፡ መኳንንት ፥
አንዠት ፡ መግለጥ ፡ ቢቻል ፡ ልብንም ፡ መክፈት ፥
ማዘን ፡ መንገብገቤን ፡ ላንት ፡ ባሳየኹት ።
የግድ ፡ ነውና ፡ በሞት ፡ መለየት ፥
በጸሎቴ ፡ ምልጃ ፡ ማታና ፡ ጠዋት ፥
ነፍስኽን ፡ ያኑራት ፡ አምላክ ፡ ከገነት ።

ስምዖን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

---

ፈገግታኽ ፡ ለስላሳ ፥ ሣቅኽ ፡ ደስታዬ ፤
ፍቅርኽ ፡ ተገኔ ፡ ነው ፥ ድምፅኽም ፡ ተስፋዬ ፤
ትምህርትኽ ፡ ብርሃኔ ፥ ምክርኽ ፡ መድኀኒቴ ፤
ትግሥትኽ ፡ ምኞቴ ፥
የሕይወቴ ፡ መኵሪያ ፡ አንተ ፡ ነኽ ፡ አባቴ ።
አባብዬ ፡ ጨዋወ ፥ አባብዬ ፡ ደጉ ፥
ጨዋታኽ ፡ ናፈቀኝ ፥ ተረቱና ፡ ሣቁ ።
ቀን ፡ ሲጨልምብኝ ፥ ኑሮ ፡ ሲሰለቸኝ ፡
ይበቃኝ ፡ ነበረ ፡ መንፈሴን ፡ ለማደስ ፡ ልቤን ፡
ለመሙላት ፥
በስልክ ፡ ደውዬ ፡ ድምፅኽን ፡ መስማት ።

ድልወንበራ ፡ ነጋ ።

---

አይረሳም ፡ ዠግና ፥ መሥዋዕት ፡ የኾነ ፥
በልጅነት ፡ ዕድሜ ፡ አገርን ፡ ያዳነ ፤
ገና ፡ ጎሕ ፡ ሲቀድ ፡ በጧት ፡ በማለዳ ፡
ተነሣ ፡ ከገነት ፡ ላርበኝነት ፡ ሜዳ ።
ሸዋና ፡ ወለጋ ፡ ባሌና ፡ ጎጃም ፥
ተሻግሮም ፡ በሱዳን ፡ መዲና ፡ ካርቱም ፥
ሰንደቅ ፡ ዓላማውን ፡ አላስነካም ፡ ብሎ ፥
ካንጋፋው ፡ ዐርበኛ ፡ ተሰልፎ ፡ ውሎ ፥
ከነዘውዴ ፡ አስፋው ፡ ከነአበበ ፡ አረጋይ ፥
ድልን ፡ ይዞ ፡ ገባ ፡ አዲሱ ፡ አደባባይ ።
ለሀገር ፡ መሠዋት ፡ በጦር ፡ ሜዳ ፡ አያልቅም ፤
በሰላሙም ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ አላረፈም ።

ያዲስ ፡ ድል ፡ አበባን ፡ ገና ፡ ሳይለምዳት ፥
የጦር ፡ አስተዳደር ፡ አዘዘው ፡ መንግሥት ።
አስተዳደርንም ፡ ይዞት ፡ ነበር ፡ ከልብ ፤
ዐነጸ ፡ ለኢትዮጵያ ፡ የሰራዊትን ፡ ደንብ ።
ባሕረ ፡ ኤርትራ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ድንበር ፥
በጠላት ፡ ተይዛ ፡ ስትንፈራፈር ፥
ቆሜ ፡ አላይም ፡ ብሎ ፡ ከግብር ፡ ተነሣ ፤
አስመራ ፡ ዘለቀ ፤ በትሩን ፡ አነሣ ።
ወጣት ፡ ሽማግሌን ፡ ሰብስቦ ፡ በሸንጎ ፥
ሀገር ፡ ተባበረው ፤ አንድ ፡ ኾነ ፡ ለበጎ ።
እባሌም ፡ ተላከ ፡ አገር ፡ ሊያስተዳድር ፤
ውጋዴን ፡ ተላከ ፡ ድንበርን ፡ ሊያስከብር ፤
የጦር ፡ መኰንን ፡ ነው ፥ ሥልጡን ፡ ወታደር ፥
ተመልሶ ፡ ገባ ፡ እጦር ፡ ሚኒስቴር ።
አውራው ፡ አበበ ፡ ነው ፥ ርሱ ፡ ተከታይ ፥
ምክሩ ፡ ያበከረ ፥ ግብሩ ፡ የሚቈይ ።
በጎንደር ፡ ተሾመ ፡ ስሜን ፡ በጌምድር ፤
አዘዞ ፡ ደረሰ ፥ ሥራ ፡ ሊዠምር ።
ምክር ፡ ቤትም ፡ ገባ ፡ መልሶ ፡ ዐዲሳባ ፤
ቆመ ፡ ለደኻው ፡ ሕዝብ ፥ ኑሮው ፡ ለተዛባ ።
በደቡብ ፡ ኢትዮጵያም ፥ ሲዳሞ ፥ አዋሳ ፥
ፍትሕ ፡ እንዳይቀርበት ፡ ሊታገል ፡ ተነሣ ።
የልቡን ፡ ሳይጨርስ ፡ ለኔ ፡ ብጤ ፡ ድርጎ ፥
ያገር ፡ ወኪል ፡ ተብሎ ፡ ኺድ ፡ አሉት ፡ ሞሮኮ ።
የነጋ ፡ ተሰጥዎ ፡ በዚህ ፡ አልተገታም ፤
በዘመድ ፡ አዝማዱ ፥ በጎረቤት ፡ ዘንድም ፡
በጓደኞች ፡ ፍቅር ፥ በቤተሰብ ፡ ኑሮው ፥
ቸር ፡ ነፍሰ ፡ ነበረው ፤ ገር ፡ ነበር ፡ ልቦናው ።
ደኻም ፡ ሲያይ ፡ አይችልም ፤ ያመዋል ፡ ልቡን ፤
ለሰው ፡ ያለው ፡ ፍቅር ፡ የለውም ፡ ወሰን ።
ምን ፡ ብዬ ፡ ልናገር ፡ ስለሰው ፡ አፍቅሮው ፤
ዐብሮ ፡ በቀሉ ፡ ነው ፥ መንትያ ፡ ተፈጥሮው ።
ምነው ፡ ቸኰልክ ፡ ዛሬ ፥ ያልለመደብኽን ፧
አገሬ ፡ ከገባኹ ፥ በቃኝ ፡ ብለኽ ፡ ይኾን ፧
የንግሊዙ ፡ ስደት ፡ አድክሞኽ ፡ ነበር ፥
የኢትዮጵያ ፡ ጣረ ፡ ሞት ፡ ሲነገር ፡ ዘወትር ።
ዛሬ ፡ ዐቅም ፡ አነሰኽ ፤ ቈረጠ ፡ ልብኽ ፥
ተለይተኽ ፡ ኼደኽ ፥ ብቻኽን ፡ ቆመኽ ፥
ለግዜር ፡ ለመናገር ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ ኾነኽ ።

ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ነጋ ።

የልጇን ፡ ወሮታ ።

አንድ ፡ ቀን ፡ ሳያምኽ ፡ የጠና ፡ በሽታ ፥
እንዳትጕሳቈል ፡ እንዳትንገላታ ፡
አገርኽ ፡ አገባኽ ፡ የሥላሴ ፡ ዕለታ ።
ያፈቀርከው ፡ አምላክ ፡ የምትወደው ፡ ጌታ ፡
አዘጋጅቶ ፡ ጠራኽ ፡ ላንተ ፡ ልዩ ፡ ቦታ ።
ዘወትር ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዳልክ ፡ በትዝታ ፥
ሳልደርስልሽ ፡ ቀረኹ ፡ እናቴ ፡ ይቅርታ ፡
እያልክ ፡ እንደ ፡ ተከዝክ ፡ እንዳዘንክ ፡ ጧት ፡ ማታ ፡
ርሷም ፡ ሠላሳ ፡ ዓመት ፡ ሳትሰጥኽ ፡ ፋታ ፡
በዘጠና ፡ ዓመትኽ ፡ ሳታስበው ፡ ጠርታ ፡
ያርበኛዋን ፡ ልጇን ፡ ከፈለች ፡ ወሮታ ።
እመደበችልኽ ፡ የማዕርግ ፡ መኝታ ፡
ዐፈሯን ፡ አልብሳ ፡ በክቡር ፡ ሰላምታ ፡
አሰናበተችኽ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ቦታ ።

የኔ ፡ አባብዬ ፡ ባለኽበት ፡ የማምዬና ፡ የልጆችኽ ፡
ፍቅር ፡ ይከተልኽ ፥ አሜን ።

አባብዬ

አልገባኝም ፡ እንጂ ፡ ሲያቃዠኝም ፡ ከርሟል ፤
ለካስ ፡ ያንተ ፡ መኼድ ፡ መሰናበት ፡ ኖሯል ።
ናፈከኝ ፡ ብልኽስ ፡ አኹን ፡ ምን ፡ ያደርጋል ፧
አባብዬ ፡ የኔ ፡ ትተኸኝ ፡ ኼደኻል!
ያንተ ፡ ነፍስ ፡ ወደዚያ ፡ የኔም ፡ እዚህ ፡ ቀርቷል ፤
ትኵር ፡ ብዬ ፡ ሳስብ ፡ ድምፅኽ ፡ ይሰማኛል ፤
አይዞሽ ፡ ባንቺ ፡ በርቺ! ፡ ያልከኝ ፡ ይመስለኛል ።

ስንብት

ሲሸኙኽ ፡ አልነበርኩ ፡ በወግ ፡ ስትቀበር ፤
እመጣለኹ ፡ ቈየኝ ፡ ብዬኽ ፡ እኮ ፡ ነበር ፧
እንደማይሳካ ፡ እንደማልኖር ፡ ባገር ፡
እኔ ፡ ሳልረዳው ፡ አንተ ፡ ዐውቀኸው ፡ ነበር ፤
እንግዲህ ፡ ምን ፡ ልኹን ፡ የታዘዘው ፡ አይቀር!
መንገድኽን ፡ ያቅናው ፤ አምላክ ፡ ይቀበልኽ ፤
የቤቱን ፡ በር ፡ ከፍቶ ፡ እጕኑ ፡ ያስቀምጥኽ ፤
የልጅኽም ፡ ፍቅር ፡ መቼም ፡ ይከተልኽ ።

ማናለብሽ ፡ ነጋ ።

በሌሊት ፡ መሥዋዕት ፡ ቀን ፡ የዋጀው ፡ ኀይል ፥
ተነሡ! ተነሡ! ስሙ ፡ ተጠርቷል ።
ለዘላለም ፡ ሰላም ፥ ለዘላለም ፡ ፍቅር ፡
ነጋ ፤ ብርሃን ፡ ኾነ ፤ ሐዘናችን ፡ ይቅር ።

***

ያች ፡ ረቂቅ ፡ ነፍስኽ ፡ ዐረገች ፡ ላይ ፡ ገነት ፤
ያ ፡ ሸበላ ፡ ሥጋኽ ፡ ዐረፈ ፡ ታች ፡ ገነት ፤
ከነጋ ፡ እኔም ፡ በኼድኩ ፥ እንዲህ ፡ ለመለየት ፥
እስኪገጣጥመን ፡ የትንሣኤው ፡ ዕለት ።

***

እናትኽም ፡ እኅትኽም ፡ ወዳጅኽም ፡ አንድነት ፡
ከፈይ ፡ ናት ፡ ስንላት ፥ ወርቅ ፡ ናት ፥ ወርቅ ፡ ናት ፤
እንደ ፡ ምን ፡ ፈትነኽ ፡ እንዴት ፡ አፈሰስኻት ፨

***

አንቺ ፡ ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ የዠግና ፡ እመቤት ፥
ተነጠልሽ ፥ ተለየሽ ፥ ተዘጋሽ ፡ እቤት ፤
ጥንትም ፡ አንድያዋ ፡ ነበርሽ ፡ ወይዘሪት ።

***

ያንተ ፡ ልጆችማ ፡ መቼ ፡ ሰባት ፡ ብቻ ፤
ጧት ፡ የዘራኻቸው ፡ ባርበኛ ፡ ዘመቻ ፡
አፍርተው ፡ ደርሰዋል ፡ ለድራር ፡ ራቻ ።

***

ግርማኽ ፡ አስደንጋጭ ፡ ነው ፥ ዝናኽ ፡ የማይደብስ ፥
ፈረስኽ ፡ ዐምባላይ ፥ አንተ ፡ አባ ፡ ይባስ ።

***

እየመራ ፡ ስምኽ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ግብር ፥
በኼድክበት ፡ ኹሉ ፡ ያ ፡ ጨለማ ፡ ጠር ፡
ዘወትር ፡ ሲከተልኽ ፡ በስደት ፡ ባገር ፥
ኹል ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ቃጣ ፡ ሊያጠፋኽ ፡ ቢችል ፥
ኹል ፡ ጊዜም ፡ ጠባቂኽ ፡ የሥላሴ ፡ ኀይል ፥
ክንዱን ፡ ዘርግቶልኽ ፥ ከልሎኽ ፡ መኻል ፥
እየሣቅኽ ፡ ተሻገርክ ፥ ውስጥኽ ፡ ቢደማም ፤
ሞት ፡ ጦሙን ፡ ዐደረ ፤ አላገኘኽም ።

***

ሕይወትኽ ፡ መጽሐፍ ፡ ታተመ ፡ ቢሉን ፥
ድንገት ፡ ጨለመብን ፡ ሳናነብ ፡ ዐብረን ።
ታሪክኽ ፡ ሕያው ፡ ነው ፥ ሥራውም ፡ ኀያል ፤
ተሰበረ ፡ ሲሉት ፡ ርሱ ፡ እሚቀጥል ፤
ሐመልማለ ፡ ገነት ፥ ጻድቅ ፡ ነኽ ፡ ልበል ፤
በልቤ ፡ ስንክሳር ፡ ይጻፍልኽ ፡ ገድል ፦
*ሚያዝያ ፡ 30 ፡ ቀን ፡ ተወለደ ፡ ነጋ ፥*
*የኹሉም ፥ ለኹሉም ፥ በኹሉም ፡ ዜጋ ፡*
*ፍትሕ ፥ ርትዕ ፥ እግዚእና ፡ እንዲከብሩ ፡ አንድጋ ።*
*ሐምሌ ፡ 16 ፡ ቀን ፡ ሌት ፡ ዐረፈ ፡ ነጋ ፥*
*ሥራውን ፡ ጨርሶ ፡ መዝገቡን ፡ ሲዘጋ ።*
*ገብርኤል ፡ ክንፎቹን ፡ ሲያጥፍ ፡ ሲዘረጋ ፥*
*ሐምሌ ፡ 19 ፡ ቀን ፡ አፈርጥም ፡ ነጋ ።*

***

ነገር ፡ ሲጨልም ፥ ሲዋዥቅ ፡ ፍጥረት ፥
ዐርበኞችን ፡ ጠቅሰኽ ፦ *ድል ፡ ማለት ፡ በውነት ፥*
*የተስፋን ፡ ሬሳ ፡ ተራምዶ ፡ እሚያዩት ፥*
ስትል ፡ ያስተማርከው ፥ ዛሬ ፡ ቢደርሰን ፥
ውሎ ፡ ዐድሮ ፡ ተረዳን ፤ እኛም ፡ ተራመድን ።

ወሴ ፡ ነጋ ።

---

ነጋ ፡ ነጋ ፡ እያለ ፡ በተስፋ ፡ የኖረ ፥
ቀኑ ፡ ጨለመበት ፡ አለ ፡ መሪ ፡ ቀረ ።
ወፎቹም ፡ ጭጭ ፡ አሉ ፤ ሆዳቸው ፡ ዐረረ ፤
ዶሮም ፡ አልጮኽ ፡ አለ ፤ ድምፁ ፡ ተሰበረ ፤
በጠዋት ፡ በማለዳ ፡ ነጋ ፡ ማለት ፡ ቀረ ።

አውሳቤ ፡ ነጋ ።

---

# "ክቡር ፡ ሞቱ ፡ ለጻድቅ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ። "



የክቡር ፡ ሊ. ፡ ገኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ቀብር ፡ ሥርዐት ፥
ሐምሌ ፡ 19 ፡ ቀን ፡ 2000 ፡ ዓ.ም. ፥
ዐዲስ ፡ አበባ ፡ እመንበረ ፡ ጸባኦት ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፥
ቤተ ፡ ሰብ ፡ ቤተ ፡ ዘመድ ፥ ወዳጅ ፡ ወገን ፥ ብዙ ፡ ሕዝብ ፡ በተገኘበት ፥
ባርበኞች ፡ ዐጀብ ፥
በተዋሕዶ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዐት ፡ ተፈጽሟል ።
ይህን ፡ ለፈጸመ ፡ ለልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ፥
ለዘላለሙ ፡ አሜን ❖

(ዐምስተኛ ፡ ዕትም ። )

©የሊ. ፡ ገኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ቤተ ፡ ሰብ ፥ ነሐሴ ፡ 2000-ነሐሴ ፡ 2001 ፡ ዓ.ም. ።